# ኢፕድ አዲስ ዘመን

ሰኞ 84ኛ ዓመት ቁጥር 041 ጥቅምት 11 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# አሳሳቢው የቁልፍ መሠረተ ልማቶች የሳይበር ጥቃት

ማህሌት ብዙነህ

ዜና ትንታኔ

የዓለም ኢኮኖሚክ ፎረም መረጃ እ.አ.አ. በ2024 እንዳሰፈረው በዓለማችን እየተከሰቱ ካሉና በቀጣይ 10 ዓመታት ከሚከሰቱ ከፍተኛ አደጋዎች ውስጥ የሳይበር ጥቃት አንዱና ዋነኛው ነው። ዓለማችን በሳይበር ጥቃት ሳቢያ እ.አ.አ በ2022 ብቻ የ8 ነጥብ 44 ትሪሊዮን ዶላር ኪሳራ አጋጥሟታል። እ.አ.አ. በ2027 ደግሞ ኪሳራው በ282 በመቶ አድጎ ወደ 23 ነጥብ 84 ትሪሊዮን ዶላር እንደሚያሻቅብ መረጃው ያመለክታል።

በኢትዮጵያ በ2015 ዓ.ም ስድስት ሺህ 959 የሳይበር ጥቃት ሙከራዎች እንደተሰነዘሩባት አስታውቃለች። ቁጥሩ በ2016 ዓ.ም ወደ ስምንት ሺህ 854 ከፍ ብሏል፡፡ ይህም የሚያሳየው የሳይበር ጥቃት በዓለም አቀፍ ደረጃም ሆነ በሀገራችን በቁጥርም ሆነ በአይነት በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ መምጣቱን ነው።

በተለይ በቁልፍ መሰረተ ልማቶች ላይ የሚሰነዘሩ ጥቃቶች በአግባቡ ካልተመከቱ ጉዳታቸው ከፍተኛ ነው። ቁልፍ የመሰረተ ልማቶቹ ሰፊ መዋእለ ነዋይ የሚጠይቁ

አሳሳቢው የቁልፍ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የናይል ወንዝ የትብብር ማሕቀፍ አንድምታ

ልጅዓለም ፍቅሬ

ዜና ትንታኔ



የናይል ወንዝ የትብብር ማሕቀፍ ባሳለፍነው ሳምንት ከእሁድ ጥቅምት ሦስት ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ሥራ እንደገባ ይፋ መደረጉ ይታወሳል። ስምምነቱ ከ11ዱ የተፋሰሱ ሀገራት መካከል ስድስቱ ሀገራት መፈረማቸውን ተከትሎም ነው ወደ ሥራ መግባቱ የታወቀው፡፡

በተለይ በስድስተኝነት ስምምነቱን ያጸደቀችው ደቡብ ሱዳን በስምምነቱ ውስጥ መካተቷ በናይል ተፋሰስ ኢኒሼቲቭ ውስጥ ያለው አጠቃላይ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ሲገለጽ ቆይቷል፡፡ ሦስት አስርት ዓመታት ገደማ የፈጀው ይህ ስምምነት የማርቀቅ፣ የድርድርና የማፅደቅ ሂደት ባሳለፍነው ሳምንት መቋጫውን ያገኘ ሲሆን፤ በውስጡም 45 አንቀጾች የያዘ

የናይል ወንዝ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል











አቶ ጥበቡ ታደሰ

# የፖለቲካ ፓርቲዎችንና በትጥቅ ትግል ላይ የሚገኙትን በምክክሩ ለማሳተፍ ጥረት እየተደረገ ነው

ዳግማዊት አበበ

አዲስ አበባ፡- የፖለቲካ ፓርቲዎችንና በትጥቅ ትግል ላይ የሚገኙትን በሀገራዊ ምክክሩ ለማሳተፍ ጥረት እየተደረገ መሆኑን የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አስታወቀ፡፡

የኮሚሽኑ ቃልአቀባይ አቶ ጥበቡ ታደሰ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኮሚሽኑ ሀገራዊ ምክክሩ ሁሉን አካታችና አሳታፊ እንዲሆን በትኩረት እየሰራ ይገኛል፡፡

በሀገሪቱ የሚገኙ የተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲዎችና በትጥቅ ትግል ላይ ያሉ አካላት ወደ ምክክሩ እንዲመጡ ጥረት እየተደረገ መሆኑን አመላክተዋል።

በሀገራችን ከሚገኙ የፖለቲካ ፓርቲዎች አብዛኞቹ ከሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ጋር

የፖለቲካ ፓርቲዎችንና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




# ማን እንደሀገር!

**ቃልኪዳን አሳዬ**

ከጊዜ ወደ ጊዜ ስር እየሰደደና ዜጎችን ለአስከፊ የሰብዓዊ መብት ጥሰትና እንግልት እየዳረገ ይገኛል። በሕገወጥ መንገድ ድንበርን በመሻገር የተሻለ ሕይወትን በመሻት በሚደረገው ጉዞ ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ ዜጎች ለስቃይ፣ ለእንግልት፣ ለጉልበት ብዝበዛ፣ ለአካል ጉዳትና ለሞት እየተዳረጉ ይገኛል።

አንዳንዶች በመንግሥት ጥረት ወደሀገራቸው ሲመለሱ ሌሎች ደግሞ በማረሚያ ቤት ስቃይና በተለያዩ እንግልት ጊዜያቸውን ያሳልፋሉ።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲ ሥራዎቹ በርካታ ዜጎችን በተለያዩ ሀገራት ከሚያጋጥማቸው ችግሮች ደህንነታቸው ተጠብቆ እንዲመጡ እያደረገ ይገኛል። ከሰሞኑ በመካከለኛው ምሥራቅ የተከሰተውን አለመረጋጋት ተከትሎ ዜጎችን ከሊባኖስ ወደሀገራቸው ለመመለስ በተደረገው እንቅስቃሴ 51 ዜጎችን መመለስ ተችሏል፡፡

ከተመላሾች መካከል አንዷ የሆነችው ባይሴ ኢንኪ፤ በቤሩት ለሰባት ዓመታት ያህል ቆይታለች፡፡ ታዲያ በእነኝህ ሁሉ የስደት ዓመታት ህይወት እንዳሰበችውና እንዳለመችው አልሆነላትም፡፡ ቤተሰቦቿንና ዘወትር የምትናፍቃቸውን የአብራኳ ክፋይ የሆኑ ልጆቿን አንዴም እንኳን ወደ ኢትዮጵያ ጎራ ብላ እንዳልጠየቀቻቸው ትገልጻለች፡፡

“የቤተሰቦቼን ናፍቆት ለመግለጽ ቃላት ያጥረኛል። በተለይም የልጆቼ ከባድ ነበር” የምትለው ባይሴ፤ እዚህ የሚወራው ወደውጭ ከተወጣ በቀላሉ ህይወት እንደሚቀየር ነው፡፡ ቋንቋ፣ የዜጎች የአኗኗር ዘይቤ፣ የሥራ ብዛትና ሌላም ህይወትን ከባድ ያደርገዋል፡፡ የሰው ቤት መስራቱ አንድ ችግር ሆኖ ሳለ በስደት ወቅት ደግሞ ሴትነት ሌላ ችግር ነው ትላለች።

ስሄድ በሕገወጥ ደላላ ነው የሄድኩት፡፡ ሄጄ በገባውበት ቤት የሚከፈለኝ ክፍያ ልጆቼን እንኳን ለመደጎም ያላስቻለኝ በመሆኑ በተደጋጋሚ አማራጮችን ስፈልግ ነበር ስትል ታስረዳለች።

በአሁኑ ወቅት ህይወታቸውን ለመቀየር በርካታ ዜጎች በስደት ምክንያት ከሀገራቸው እየወጡ ነው፡፡ ነገር ግን የስደት ላይ ህይወት እዚህ ሁነን እንደምናስበው ቀላል አይደለም፡፡ በእኔ ይብቃ ማን እንደሀገር! በሀገር መኖርን የሚመስል ነገር የለም። ምንም ቢሆን በሀገራችን ላይ ያገኙትን ሥራ ሰርቶ መኖር ይሻላል ስትል ባይሴ ትመክራለች፡፡

የናፈቅኳትን የሀገሬን ምድር ስረግጥ ልዩ የሆነ ስሜት ተሰምቶኛል፡፡ ይህ እንዲሆን ሁሌም ለፈጣሪዬ ጸሎት እያደረግሁ ነበር የምትለዋ ባይሴ ኢንኪ፤ ብዙ አደጋና ችግር አልፌ እዚህ ሀገሬ ስደረስ ሞቼ እንደተነሳሁ ነው የምቆጥረው በማለት ደስታዋን ትገልጻለች፡፡



**የመጀመሪያው ዙር ከሊባኖስ ተመላሽ ዜጎች ሀገራቸው ገብተዋል**

እንደ ባይሴ ኢንኪ ሁሉ ከባድና አስከፊ ጊዜያትን እንዳሳለፈች በቁጭት የምትናገረው ሌላኛዋ ከሊባኖስ ተመላሺዋ ዝናሽ ገተሌ ናት፡፡

ከነበረው የከፋ ችግር በሰላም ወደሀገራቸው እንዲመለሱ በቆንጽላ ጽህፈት ቤቱ አማካኝነት ተመዝግበው እስከ ኤርፖርት ድረስ ተገቢው ሽኝት እንደተደረገላቸው በማንሳት፤ የተደረገላቸውን ትብብር በአዎንታ በመመልከት አመስግናለች፡፡

እንደ ዝናሽ ገተሌ ንግግር፤ ያሰቡትን አለማሳካት፤ እንደሄዱ አለመመለስ የሕገ ወጥ ስደት ትርፉ ነው። ዜጎች በሕገወጥ አዘዋዋሪዎች የሀሰት ማማለያ ተታለው ያላቸውን ጥሪት ሸጠው እና ተበድረው ህይወታቸውንም ለአደጋ አጋልጠው ወደ ሳዑዲ አረቢያና ሌሎች ሀገራት በተለያዩ መንገዶች የተሻለ ኑሮና ሥራ ፍለጋ ይሄዳሉ፤ ዛሬም በዚህ መንገድ ጉዞው ቀጥሏል፡፡

ሊባኖስ በነበርንበት ወቅት የነበረው ችግር መድረሻ እስኪታጣ ድረስ የሚያስጨንቅ ነበር በማለት ያሳለፈችውን ከባድ ጊዜ የምታስታውሰው ዝናሽ፤ ከዛ ሁሉ ችግር አልፎ ለሀገር መብቃትን ማሰብም እንደሰማይ የራቀ መሆኑን በመከፋት ታወሳለች፡፡

ዝናሽ ገተሌ፤ በተጨባጭ እየተከናወነ ያለውን ሁኔታ ለመግለጽ ከባድ ነው፡፡ ብዙዎቹ ለሀገራቸው ምድር ሳይደርሱ አፈር ውስጥ የገቡ እህቶቻችን አሉ፡፡ ከዛ ውስጥ ተርፌ ሀገሬ እገባለሁ የሚል እሳቤ በፍጹም አልነበረኝም፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ቸርነት የሀገሬን ምድር ረግጫለሁ ትላለች፡፡

አሁንም በሊባኖስ የሚኖሩና በጭንቅ ያሉ በርካታ ኢትዮጵያውያን መኖራቸውን የምታነሳዋ ዝናሽ ገተሌ፤ ወገን ለወገን ደራሽ ነውና መንግሥት ለእነሱ የሰጣቸውን አይነት ትኩረት ለሌሎቹም በመስጠት እንዲታደጋቸው ትጠይቃለች፡፡

በመጀመሪያው ዙር 51 ዜጎች ወደሀገራቸው በገቡበት ወቅት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር ነቢያት ጌታቸው እንደተናገሩት፤ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በሚያካሂደው የዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲ በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ ዜጎችን ደህንነት እየተከታተለ ችግሮች ሲያጋጥሙ መፍትሄዎችን እያስቀመጠ ሲሠራ ቆይቷል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለይም በሊባኖስ የተፈጠረውን ቀውስ ተከትሎ በርካታ ዜጎች ለችግር ተጋላጭ መሆናቸውን ይናገራሉ፡፡ ይህ ችግር እንደተሰማ በሚኒስቴሩ የሚመራ ብሄራዊ ኮሚቴና አፋጣኝ የቴክኒክ ኮሚቴ በማቋቋም ለችግሩ መፍትሄ ለመስጠት የተለያዩ እንቅስቃሴዎች በማከናወን ላይ ይገኛል ይላሉ።

በዚህም በአካልና በዲጂታል የምዝገባ ሥርዓት ተዘርግቶ ዜጎች እየተመዘገቡ ይገኛሉ ያሉት አምባሳደር ነቢያት፤ ዜጎች ሊባኖስ በሚገኘው ቆንስላ ጽህፈት ቤት አማካኝነት በፈለጉት አማራጭ ተመዝግበው ወደሀገራቸው እንዲመለሱ ጥሪ አቅርበዋል።

እስካሁን ከሶስት ሺህ በላይ ዜጎች በተለያዩ መንገዶች በቆንስላ ጽህፈት ቤቱ እንዲመዘገቡ የተደረገ ሲሆን፤ ወደ ሀገራቸው የመመለስ ሥራ የሚቀጥል ይሆናል ሲሉ ያስረዳሉ።

ከዚህም ባለፈ የአደጋ ተጋላጭነት ስጋት ያለባቸው አንፃራዊ ደህንነት ወደሚገኝበት ቦታ እንዲንቀሳቀሱ እየተደረገ መሆኑንም አምባሳደር ነብያት ይጠቁማሉ።

እንደ አምባሳደር ነቢያት ከሆነ፤ ዜጎቹን ለመመለስ እየተደረገ ባለው ጥረት የሚያስተባብር አመራር ወደ ሊባኖስ ተልኮ ሥራውን ጀምሯል። የመጡትንም ሆነ ገና የሚመጡ ዜጎችን ከቤተሰቦቻቸው ጋር ለማገናኘት የሚያስችል አሠራር ተዘርግቷል፡፡

ዛሬም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ኢትዮጵያውያን በተለያዩ ሀገራት በስቃይ ላይ ይገኛሉ፡፡ ዜጎች የሕገወጥ ዝውውር ሰለባ እንዳይሆኑ የመንግሥት ተቋማት ከሚሠሩት ሥራ ያለፈ ሕዝባዊ ምላሽ ይሻል። እንደ መንግሥትና ሕዝብ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር በዜጎች፣ በህብረተሰብ እና በሀገር ላይ እያደረሰ ያለውን ጉዳት ከግንዛቤ ያስገባ የመከላከል ሥራ ለነገ የማይባል ነው፡፡

# በኅዳር የዓይን ብሌን ልገሳ ወር ይከበራል

## - በሩብ ዓመቱ 75 የዓይን ብሌን ተሰብስቧል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የማህበረሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ መጪውን ኅዳር ወር የዓይን ብሌን ልገሳ ወር ሆኖ እንደሚከበር የኢትዮጵያ የደምና ሕብረ ሕዋስ ባንክ አገልግሎት አስታወቀ፡፡ በ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት 75 የዓይን ብሌን ብቻ መሰብሰብ መቻሉም ተጠቁሟል፡፡

የአገልግሎቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀብታሙ ታዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የዓይን ብሌን ልገሳ ላይ የማህበረሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ መጪው ኅዳር ወር በተለያዩ ዝግጅቶች ይከበራል፡፡

ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ውስጥ የሚገኝ አንድ የዓይን ባንክ ብቻ መኖሩ የተደራሽነት ችግር ፈጥሯል ያሉት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ የዓይን ብሌን የማሰባሰብ ሥራው በአዲስ አበባ በሚገኙ ጥቁር አንበሳ፣ ቅዱስ ጳውሎስና ራስ ደስታ ሆስፒታሎች ብቻ እየተከናወነ መሆኑን ጠቁመዋል። ይህም ለማህበረሰቡ ግንዛቤ ለመፍጠርና በቂ የዓይን ብሌን ለመሰብሰብ ተግዳሮት ሆኗል ብለዋል፡፡

በተያዘው ዓመት ቢያንስ ከአዲስ አበባ ውጪ በሚገኝ አንድ ሆስፒታል ተጨማሪ የዓይን ባንክ ለመክፈት መታቀዱን አስታውቀው፤ ለዚህም ከአገልግሎቱ የዓይን ብሌን ወስደው ንቅለ ተከላ የሚሠሩ ጅማ፣ ጎንደር፣ መቀሌና ሐዋሳ ያሉ ሆስፒታሎች ላይ የዳሰሳ ጥናት እየተሠራ መሆኑን አንስተዋል።

በተያዘው በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት 75 የዓይን ብሌን የመሰብሰብ ሥራ መሠራቱን ጠቅሰው፤ እንደ ሀገር ያለው የዓይን ብሌን ንቅለ ተከላ ፍላጎት ግን ከፍተኛ ነው፡፡ የዓይን ብሌን የሚለግሱ ሰዎችን ቁጥር ማሳደግ አስፈላጊ ነው ሲሉ አስረድተዋል፡፡

በመጪውን ኅዳር የተለያዩ ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበት የዓይን ብሌን ልገሳ ወር በማካሄድ የግንዛቤ ፈጠራ ሥራ ለመሥራት ዝግጅት እየተደረገ ነው ብለዋል፡፡

የዓይን ባንክ ተደራሽነት እጥረት ተከትሎ ማህረሰቡ የዓይን ብሌን ለመለገስ ያለው እንቅስቃሴ ዝቅተኛ መሆኑን አስታውሰው፤ የህብረተሰቡን ተሳትፎ ለማሳደግ የደም ልገሳ መርሀ ግብር በሚከናወንባቸው ቦታዎች ላይ ዓይን ብሌን ቃል መግባትን አስተሳስሮ እንዲሠራ እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል።

ከዚህ በፊት ዓይን ብሌን ንቅለ ተከላ ሕክምና




የተሰጣቸው ሰዎች ከመሠረቱት ማህበር ጋር በመተባበርም የግንዛቤ ፈጠራ ሥራውን ለማከናወን ጥረት እንደሚደረግ ተናግረዋል፡፡

በዓይን ብሌን ጠባሳ ምክንያት የዓይን ብርሃናቸውን አጥተው የተለያዩ ችግሮች ውስጥ የሚገኙ በርካታ ዜጎች መኖራቸውን አንስተው፤ የዓይን ብሌን የሚለገሰው ከሕልፈት ሕይወት በኋላ በመሆኑ በሕይወት እያለን ቃል ገብተን ለሌሎች ብርሃን እንስጥ ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡



አቶ ታሪኩ በላቸው

# አገልግሎቱ የገበያ ድርሻውን 50 በመቶ ከሀገር ውስጥ አምራቾች የመሸፈን ፍላጎት አለው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በሶስት ዓመታት ውስጥ 50 በመቶ የመድኃኒት አቅርቦት የገበያ ድርሻውን ከሀገር ውስጥ አምራቾች ለመሸፈን ፍላጎት እንዳለው የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት አስታወቀ።

የአገልግሎቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ታሪኩ በላቸው ለኢፕድ እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት ጥራታቸው የተረጋገጡ መድኃኒቶችና የህክምና መገልገያዎችን በተመጣጣኝ ዋጋ ቀጣይነት ባለው መልኩ ለጤና ተቋማት ያቀርባል።

በአገልግሎቱ ስትራቴጂክ እቅድ መሰረት ለሀገር ውስጥ መድኃኒት አምራቾች 60 በመቶ የገበያ ድርሻ ለመስጠት ታቅዷል ያሉት አቶ ታሪኩ፤ የተያዘው ዓመትን ጨምሮ በሶስት ዓመት ውስጥ የሀገር ውስጥ መድኃኒት አምራቾች የአገልግሎቱን 50 በመቶ የገበያ ድርሻ እንዲሸፍኑ ፍላጎት መኖሩን ተናግረዋል።

አሁን ላይ አገልግሎቱ ለጤና ተቋማት ከሚያቀርበው መድኃኒቶች ውስጥ 30 በመቶ የሚሆነው የገበያ ድርሻ በሀገር ውስጥ መድኃኒት አምራቾች እየተሸፈነ መሆኑን የገለጹት አቶ ታሪኩ፤ ይህን ወደ 50 በመቶ ለማሳደግ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ ከመድኃኒት አምራቾችና አስመጪዎች ማህበር እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየተሰራ እንደሆነ አንስተዋል።

የዕቅዱ ዋና ዓላማ ከውጭ በሚገቡ መድኃኒቶች ላይ ያለውን ጥገኝነት ለመቀነስ እና የሀገር ውስጥ ምርትን ለማሳደግ እንዲሁም አምራቾችን ለማበረታታት ነው ብለዋል።

አቶ ታሪኩ እንደተናገሩት፤ውጥኑ የሀገር ውስጥ የመድኃኒት አምራቾች በገቢ ደረጃ እንዲሻሻሉና ከዓለም አቀፍ የመድኃኒት አምራች ኩባንያዎች ጋር በብቃት እንዲወዳደሩ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።

ለሀገር ውስጥ የመድኃኒት አምራቾች 50 በመቶ የገበያ ድርሻ ማግኘት ለሀገሪቱ በርካታ ጥቅሞችን ያስገኛል ያሉት አቶ ታሪኩ፤ ከእነዚህም መካከል ከውጭ በሚገቡ ምርቶች ላይ ያለውን ጥገኝነት ለመቀነስ፣ ለስራ እድል ፈጠራ፣ በተመጣጣኝ ዋጋ መድኃኒቶችን ተደራሽ ለማድረግ እንደሚረዳ አስረድተዋል።

ባለፉት ዓመታት ከ90 በመቶ በላይ የሚሆነው የአገልግሎቱ የመድኃኒት ግዢ የሚፈጸመው ከውጭ ሀገራት ነው ያሉት አቶ ታሪኩ በላቸው፤ ይህም የሀገር ውስጥ መድኃኒት አምራቾች በሀገሪቱ የመድኃኒት አቅርቦት ገበያ ላይ ያላቸው ድርሻ ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል ብለዋል።

መድኃኒቶችን ከውጭ ሀገራት ገዝቶ ለማምጣት የውጭ ምንዛሪ እጥረት እንደሚያጋጥም ጠቁመው፤ አምራቾቹ ከቻይና፣ ከህንድና ከተለያዩ የአውሮፓ ሀገራት በመሆናቸው ትራንስፖርት ላይ ተግዳሮቶች ያጋጥማሉ ሲሉ አንስተዋል። በተለይ መድኃኒቶች በድንገተኛና በወረርሽኝ ጊዜ በሚፈለገው ፍጥነት ለማድረስ አስቸጋሪ መሆኑን ገልጸዋል።

አገልግሎቱ በጤና ሚኒስቴር አስተባባሪነት እነዚህን ችግሮች ለመፍታትና የሀገር ውስጥ አምራቾችን ለማበረታታት በርካታ ሥራዎችን ሲሰራ መቆየቱን ጠቁመዋል። በተለይም መመሪያዎችን የማሻሻል ሥራ መከናወኑን ተናግረዋል።

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያውም ለሀገር ውስጥ መድኃኒት አምራቾች የውጭ ምንዛሪ ግኝት ጠቀሜታ እንዳለው አመላክተዋል። አገልግሎቱ በየዓመቱ በቢሊዮን ብሮች የሚገመቱ የመድኃኒት ግዢ እና ስርጭት ስራዎችን ያከናውናል።

# ዜጎች የጥላቻ ንግግርና የሐሰተኛ መረጃ ጥቆማ እንዲያቀርቡ የሚያስችል ሥርዓት በክልሎች ተዘርግቷል

**ቃልኪዳን አሳዬ**




አዲስ አበባ፡- በተያዘው በጀት ዓመት ዜጎች ስለጥላቻ ንግግርና ሐሰተኛ መረጃ ስርጭት በራሳቸው ቋንቋ ጥቆማና ቅሬታ እንዲያቀርቡ የሚያስችል አሰራር በክልሎች መዘርጋቱን የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለስልጣን አስታወቀ፡፡

በባለስልጣኑ የዋና ዳይሬክተር ጽህፈት ቤት ኃላፊ የሺወርቅ ግርማ በተለይ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ባለስልጣኑ በተያዘው በጀት ዓመት በክልሎች ቢሮ በመክፈትና ባለሙያዎችን በመመደብ ዜጎች ስለጥላቻ ንግግርና ሐሰተኛ መረጃ ስርጭት በራሳቸው ቋንቋ ጥቆማና ቅሬታ እንዲያቀርቡ፤ እንዲሁም በጉዳዩ ዙሪያ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የሚያደርግ አደረጃጀት ዘርግቷል፡፡

በጅግጅጋ፣ ድሬዳዋ፣ ጅማ፣ ሰመራ፣ ሀረር፣ አሶሳና በሌሎችም አካባቢዎች ቢሮዎች ተከፍተው በሥራ ላይ እንደሚገኙ ያነሱት ወይዘሮ የሺወርቅ፤ ተቋሙ ለሚያወጣው ሀገራዊ የጥላቻ ንግግርና የሐሰተኛ መረጃ ጥናት ሪፖርትም ከከፈታቸው ቢሮዎች ግብዓት ይወስዳል ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ የተለያዩ ቋንቋዎች የሚነገሩባትና በርካታ የሕዝብ ቁጥር ያላት ሀገር መሆኗን ጠቁመው፤ የጥላቻ ንግግርና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከልና ህብረተሰቡ ጥቆማዎችንና ቅሬታዎችን ሊያቀርብ እንደሚገባ አመላክተዋል።

ዜጎች የዳበረ የመረጃ አጠቃቀም ልምድ እንዲኖራቸው በተያዘው በጀት ዓመት ከፍተኛ የግንዛቤ ማስጨበጫና ህብረተሰቡን ተሳታፊ የሚያደርጉ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ባለስልጣኑ በአዋጅ በተሰጠው ኃላፊነት መሰረት በተለያዩ አማራጮች ህብረተሰቡ ምን አይነት መረጃዎችን ማሰራጨትና መጠቀም እንዳለበት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን እየሠራ ነው ብለዋል፡፡

ጥፋቶች ተፈጽመው ሲገኙም ከተቋማትና ግለሰቦች የሚመጡ ቅሬታዎችና ጥቆማዎችን በማጣራት ሙያዊ አስተያየት በማከል ለሚመለከተው የሕግ አካል ተደራሽ እንደሚደረግ አመላክተዋል።

ዜጎችና ተቋማት ይሄንን በመረዳት በባለስልጣኑ ነጻ የስልክ መስመር እና በተለያዩ የተቋሙ የግንኙነት ዘይቤዎች በመጠቀም ቅሬታና ጥቆማ በማቅረብ ተሳታፊ እንዲሆን ጥሪ አቅርበዋል፡፡

በበይነ መረብ የሚሰራጩ የጥላቻና ሀሰተኛ መረጃዎች ያላቸውን የጉዳት ደረጃ በመከታተል ባለስልጣኑ ሪፖርት እንደሚያወጣ የገለጹት ወይዘሮ የሺወርቅ፤ በዚህም በፖለቲካ፣ በብሄር፣ በማንነት፣ በአመለካከትና በሌሎችም ላይ በማተኮር ርዕሰ ጉዳያቸው በየጊዜው የተለያዩ የስድብ፣ የዛቻ፣ ክብረ ነክና ሌሎችም ይዘት ያላቸው መረጃዎች እየተሰራጩ እንደሆነ መገንዘብ ተችሏል ብለዋል፡፡

እንደኤክስ (ትዊተር)፣ ዩቲዩብ፣ ፌስቡክ፣ ቲክቶክና በመሳሰሉት ማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ የሀሰተኛ መረጃ ስርጭት ቁጥጥር እንዳለ አንስተው፤ በአዲስ አበባ፣ በሐዋሳ፣ በድሬዳዋና በሌሎችም የክልል ከተሞች ለዜጎች የበይነ መረብ ሚዲያዎችን ለመጠቀም የሚያስችል ነጻ የግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠቱን አስታውቀዋል።

በአዲስ አበባ ለሚገኙ የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚኒ ሚዲያ አባላትና መምህራን፣ በተጨማሪም ለፓርላማ አባላትና ለፍትህ አካላትም ስለጉዳዩ ግንዛቤ እንዲይዙ መደረጉን አንስተዋል። የግንዛቤ ፈጠራ ሥራዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ ገልጸዋል።

በቀጣይም ከሬዲዮ አድማጮችና በጋዜጠኝነት ላይ ከሚሰሩ የሙያ ማህበራት ጋር በመተባበር ዜጎች በቂ ግንዛቤ ኖሯቸው ጥሰቶች ሲገኙ እንዲጠቁሙና ቅሬታ እንዲያቀርቡ ይሠራል ብለዋል፡፡

# ከ160 ሺህ በላይ አርብቶ አደሮች የእንስሳት መድን ተጠቃሚ ሆነዋል

**መስከረም ሰይፉ**



አዲስ አበባ፡- በአርሶ አደሮች የአደጋ ቅነሳ ፕሮጀክት ከ160 ሺህ በላይ አርብቶ አደሮች በእንስሳት መድን ተጠቃሚ መሆናቸውን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ።

በግብርና ሚኒስቴር የአርብቶ አደሮች አደጋ ቅነሳ ፕሮጀክት አስተባባሪ ጀማል አሊዪ ለኢትጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሀገሪቱ በአርብቶ አደር አካባቢዎች በተደጋጋሚ በሚከሰተው ድርቅ ምክንያት በእንስሳት ሀብት ላይ የሚደርሰው ጉዳት ከፍተኛ ነው፡፡

ጉዳቱን ለመቀነስ ግብርና ሚኒስቴር ከሁለት ዓመት በፊት የጀመረው የአደጋ ስጋት ቅነሳና አካታች የኢኮኖሚ እሴት ማሻሻያ ፕሮጀክት ስር የእንስሳት መድን አገልግሎትን በማካተት አርብቶ አደሩን ተጠቃሚ እያደረገ ይገኛል።

የ2017 የአንድ ወቅት ምዝገባን ጨምሮ ከ160 ሺ በላይ አርብቶ አደሮች የእንስሳት መድን አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል ብለዋል፡፡

የአርሶ አደር አካታች የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮጀክት በአሁኑ ሰአት በአፋር ፣በሶማሌ ፣በኦሮሚያ፣ ደቡብ ኢትዮጵያና በደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ስር በሚገኙ 187 ወረዳዎች ላይ እየተተገበረ መሆኑን ተናግረዋል።

አካባቢዎቹ የሀገሪቱን 60 በመቶ የሚሆን የእንስሳት ሀብት መያዛቸውን ጠቁመው፤ ከእንስሳት ሽያጭ የሚገኘው አብዛኛው ገቢው ከእነዚሁ አካባቢዎች ጋር የተያያዘ መሆኑን አንስተዋል።

አቶ ጀማል የመድን አገልግሎቱ ከተጀመረ እስካሁን ባለው ጊዜም አርብቶ አደሮችን ለማበረታታት መንግሥት ከ140 ሚሊዮን ብር በላይ ፕሪሚየም መክፈሉን ገልጸዋል።

የእንስሳት መድን አገልግሎቱ ተጠቃሚ የሚያደርጋቸው አካባቢዎች በድርቅ የሚጠቁና የእንስሳት ሀብት ያለባቸው አካባቢዎች መሆናቸውን ጠቁመው፤ ወረዳዎቹ የ20 ዓመት የሳተላይት መረጃን መሰረት በማድረግ የተለዩ መሆናቸውን አስታውቀዋል።

በኢትዮጵያ የሚገኙ በእንስሳት ኢንሹራንስ ተጠቃሚ ሊሆኑ ይገባቸዋል ተብለው የሚታሰቡ ሁሉም ወረዳዎች ተካተዋል ማለት እንደሚቻል ገልጸዋል፡፡

የእንስሳት መድን አገልግሎቱ የክረምት ዝናብ በአግባቡ ካልተገኘ በበጋ ሶስት ወራት ማለትም ጥቅምት፣ህዳርና ታህሳስ ወራት ላይ ድርቅ ሊከሰት ይችላል ተብሎ ስለሚታሰብ በመስከረም ወር ምዝገባ የሚካሄድበት አሰራርን የሚከተል መሆኑን አንስተዋል።

ሌላኛው አሰራር ደግሞ የበልግ ዝናብ በአግባቡ ካልዘነበ በክረምት ወራት ድርቅ ሊያጋጥም ስለሚችል በየካቲት ወር ምዝገባው እንደሚካሄድ አስረድተው፤ ችግር ሲያጋጥምም በመድን አገልግሎቱ መሰረት አርሶ አደሩ በሚያገኘው ድጋፍ እንስሳቱን በመተካት ሕይወቱን እንዲመራ የሚረዳ አሰራር መሆኑን አመላክተዋል።

ዜና

# የናይል ወንዝ

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የያዘ እንዲሁም ለተግባራዊነቱ ከ11ዱ ሀገራት ስድስቱ እንዲፈርሙ መርህ የሚያስቀምጥ ነው፡፡

ስምምነቱ መጽደቁ እ.አ.አ በ1929 እና 1959 በግብጽና ሱዳን መካከል የተደረገው የቅኝ ግዛት ዘመን ስምምነት የሚቀለብስ፣ ቀጣናዊ ትብብርን የሚያጠናክርና የውሃ ሀብት አስተዳደርን በተመለከተ ሚዛናዊ አካሄድ እንዲኖር እንደሚያደርግም ይጠበቃል፡፡

የናይል ተፋሰስ የትብብር ማሕቀፍ ስምምነት ወደ ተግባር መግባቱ በዓባይ ውሃ ኢትዮጵያ ላይ የሚቀርቡ ምክንያት አልባ ክሶችን የሚያስቀር ስለመሆኑም የተደበቀ እውነት አይደለም፡፡

ስምምነቱ መጽደቁ የቀጣናው የውሃ ፖለቲካ ላይ ምን ዓይነት ተጽዕኖ ይኖረዋል? ያለውስ ፋይዳ ምንድነው? ስምምነቱ እንዲጸድቅስ የኢትዮጵያ ሚና ምን ነበር? እንዲሁም በስምምነቱ ያልተካተቱ ሀገራት ለማሕቀፉ ተፈጻሚነት የሚቋቋመው ኮምሽን ላይ እክል ሊፈጥሩ የሚችሉበት ሁኔታ አለ ወይ? ሲል ኢፕድ የዘርፉ ምሁራንን አነጋግሯል።

የድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ተመራማሪና የህዳሴው ግድብ ተደራዳሪ ቡድን የሕግ አማካሪ አምባሳደር ኢብራሂም ኢድሪስ እንደሚሉት፤ ስምምነቱ የተፋሰሱ ሀገራት እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችል እንዲሁም የቀጣናውን ልማትና ትብብር የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ስምምነቱ መጽደቁ የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ሥራ ውጤት የሚያሳይ ነው የሚሉት አምባሳደር ኢብራሂም፤ በተለይ ደቡብ ሱዳን ስምምነቱን እንድታጸድቀው ኢትዮጵያ ባለፉት ዓመታት ከፍተኛ ሚና ተጫውታለች ይላሉ፡፡

ከውሃ ፖለቲካው አንጻርም አስተማማኝ የሆነ የላይኛው ተፋሰስ ሀገራት መብት ያረጋገጠ፣ ሱዳንና ግብጾች እየሄዱበት የነበረው መንገድ ትክክል አለመሆኑ በተግባር ያሳየ ነውም ባይ ናቸው፡፡

እንደ አምባሳደር ኢብራሂም ገለጻ፤ በስምምነቱ መሠረት ስድስት ሀገራት ካጸደቁት ሕጋዊ ሆኖ በሥራ ላይ መዋል ይጀምራል፡፡ ስምምነቱን ያላጸደቁ ሀገራት ለትብብር ማሕቀፉ በሚቋቋመው ኮሚሽን የሥራ መሠናከል የሚሆኑበት አግባብ የለም፡፡

አምባሳደር ኢብራሂም እንደሚሉት፤ እ.ኤ.አ በ1959 ሱዳንና ግብጽ ባደረጉት ስምምነት መሠረት ግብጽ 55 ነጥብ አምስት ቢሊዮን እንዲሁም ሱዳን ደግሞ 18 ነጥብ አምስት ቢለዮን ኩዩቢክ ሜትር ውሃ በዓመት እንዲያገኙ የሚደነግግ መሆኑን አስታውሰው፤ ይህም በሌላ አነጋገር የሚሄደው ውሃ ሁሉ ሱዳንና ግብጽ ብቻ እንዲጠቀሙ የሚያዝ እና ሌሎቹ ሀገራት ውሃ የማግኘት መብታቸውን የሚነፍግ መሆኑን ያብራራሉ፡፡

በቅርቡ ጸድቆ ወደ ትግበራ የገባው የናይል ወንዝ የትብብር ማሕቀፍም ይህንን የበላይ ተጠቃሚነት የሚያስቀርና የቅኝ ግዛት ውሎቹን ከጥቅም ውጪ የሚደርግ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

የጋራ ተጠቃሚነት እንዲኖር ለማድረግ፣ ፍትሐዊ ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥና በላይኛው ተፋሰስ ሀገራት ላይ ሕጋዊ ጥያቄ ለማቅረብ በስምምነቱ ውስጥ መካተት ግድ በመሆኑ የናይል ወንዝ የትብብር ማሕቀፍ ስምምነት ከማንም በላይ ተጠቃሚ የሚያደርገው የታችኛው ተፋሰስ ሀገራትን ነው ያሉት ደግሞ የውሃ ሀብት ባለሙያ እና የቀድሞ የህዳሴው ግድብ ተደራዳሪ ፈቅአህመድ ነጋሽ ናቸው፡፡

ስምምነቱ ውሃ አጠቃቀም ላይ ብቻ ያተኮረ ሳይሆን የውሃ ጥበቃና እንክብካቤ፣ ቁጥጥር፣ የውሃ አስተዳደርን የተመለከተ፣ ውሃን በአግባቡ መጠቀም እንዲሁም ተጨማሪ የውሃ ሀብት ማፈላለግ የሚያግዝ መሆኑንም ነው የሚገልጹት፡፡

በማሕቀፉ ውስጥ ያልተካተቱ ሌሎች ሀገራት የውሃ አጠቃቀም መረጃ እንዲኖራቸው፣ የሀብት ክፍፍሉ ላይም ውሳኔ ሰጪ ለመሆን እንዲሁም በቀጣናው የትብብር ልማት ላይ ተጠቃሚ ለመሆን ስምምነቱን ማጽደቅ ይኖርባቸዋል የሚሉት ባለሙያው፤ አለበለዚያ በጀርባቸው የሚወሰነው ውሳኔ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድርባቸው የሚችል መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡

ባለሙያው እንደሚሉት፤ ስምምነቱን ያልፈረሙ ሀገራት መች ይቀበሉታል የሚል እንጂ አይቀበሉትም የሚል እምነት እንደሌላቸው ተናግረው፤ በተለይ ኮሚሽኑ ጠንካራ ኃላፊነት ተሰጥቶት ትላልቅ ውሳኔዎች የሚያሳልፍ ከሆነ ረጅም ጊዜ የማይፈጅ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

እንደ አቶ ፈቅአህመድ ገለጻ፤ ስምምነቱ በሀገራት መካከል የሚነሱ የተለያዩ የልማት ጫናና ስጋት ለመቀነስ፣የራስን የልማት ወሰን በትክክል ለማወቅ፣ የተለያዩ ድጋፎች ለማግኘት፣ ለልማቶቹ ዓለም አቀፍ ሕጋዊ ከለላ ለማግኘት እንዲሁም ከውሃውም ባሻገር ትብብሮችን የማጠናከር እድሎች ይኖሩታል፡፡

ድርድሩ ገና አላለቀም፤ ለቀሪው ድርድር ከወዲሁ መዘጋጀትና ኮሚሽኑም ጠንካራና ፍትሐዊ እንዲሆን የአሰራር ሥርዓቱም እንዲዘምን ማድረግ እንደሚያስፈልግ ይመክራሉ፡፡

ስምምነቱ የቅኝ ግዛት ውሎች እንዲወገዱ አስገዳጅና ከዓለም ሕግጋት ጋር የተጣጣመ ስለሆነ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ በቀላሉ እንዲቀበለው ያደርጋል ይላሉ፡፡

ስምምነቱን ያጸደቁ ሀገራት ስምምነቱን ለማስፈጸም የሚቋቋመው ኮሚሽን ውጤት እንዲያስገኝና ከሚሰነዘሩት የተለያዩ ሴራዎች ለመውጣትም ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ ያሳስባሉ፡፡

በዚህም ተባለ በዚያ ግን በጥቅሙ ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝ ላይ ያከናወነችው ዲፕሎማሲያዊ ሥራ እና የቀጣናውን ሀገራት በትብብር ማሕቀፍ እንዲስማሙ የምታደርገው ጥረት ውጤታማ ሆኗል። በቀጣይም ይህን ዲፕሎማሲያዊ ጥረትና አቅም አጠናክሮ መቀጠሉ ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራት ይገባል።

# አሳሳቢው የቁልፍ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ብሎም ለሀገር ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ዕድገት የማይተካ ሚና አላቸው። እነዚህ ተቋማት የሳይበር ጥቃት ቢደርስባቸው በሀገር ጥቅም፣ ደህንነት፣ እና በዜጎች ሕይወት ላይ ከፍተኛ ቀውስ ይፈጥራል። ኢትዮጵያም የሳይበር ጥቃትን ለመከላከል ባለሙያዎችን ከማሰልጠን ባለፈ ቴክኖሎጂ የማዘመንና የሕግ ማሕቀፎችን በማዘጋጀት እየሰራች መሆኑ ይታወቃል። በቀጣይም በቁልፍ መሰረተ ልማቶች ላይ የሚደርሱ የሳይበር ጥቅቶችን አስቀድሞ ለመከላከል በቀጣይ ምን መደረግ አለበት? በሚለው ጉዳይ ላይ የዘርፉ ምሁራን ሃሳባቸውን ሰጥተዋል።

የአንድን መረጃ ምስጢራዊነት፣ ሙሉዕነትና ተደራሽነት ላይ ማስተጓጎል ለማድረግ የሚደረግ ጥቃት ሁሉ የሳይበር ጥቃት ይባላል ያሉት በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊናና ባህል ግንባታ ዲቪዥን ኃላፊ አቶ ቢኒያም ማስረሻ ናቸው፡፡

ከመረጃ ላኪና ተቀባይ ሌላ ባልተፈቀደ መንገድ የሌላን አካል መረጃ ማየት፣ መለወጥና ፣ማውደምን የሚጨምረው ጥቃቱ፤ ከግለሰብ ጀምሮ እስከ ትላልቅ ሀገራዊ ቁልፍ መሰረተ ልማቶችና ተቋማት ድረስ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስ መሆኑን ነው ያነሱት።

እንደሀገርም የሳይበር ጥቃት ተጋላጭነት እየጨመረ መሆኑን ጠቁመው፤ ጥቃቱን አስቀድሞ ለመከላከልና ተጋላጭነትን ለመቀነስ ሀገር አቀፍ የሳይበር ደህንነት የሕግ ማሕቀፎችና የተለያዩ ፖሊሲና ስትራቴጂዎች መዘጋጀታቸውን ይገልጻሉ።

በተለይም ተቋማት እራሳቸውን ለመጠበቅ መከተል ያለባቸው መንገዶች በሰፊው ተቀምጧል ያሉት አቶ ቢንያም ፤ ከቴክኖሎጂ፣ጥቃቶችን ከመለየት ብሎም መከላከል የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎች ጨምሮ በዋናነት ተቋማት ሊያሟሏቸው የሚገቡ ዝቅተኛው የሳይበር ደህንነት ስታንዳርድ ያካተተ መሆኑን ያስረዳሉ።

በይበልጥ ለሳይበር ጥቃት ተጋላጭ የሆኑ የፋይናንስ ተቋማትና ሌሎችም የተቀመጠውን ፖሊሲ አጠቃቀም የሚመራ መዋቅርን የያዘ የአሠራር ሥርዓት በመገንባት ጥብቅ የደህንነት መስፈርቶችን መከተል እንዳለባቸው ይመክራሉ። ብሎም የሰው ኃይላቸውን የሳይበር ደህንነት ንቅተ-ህሊና ለመገንባት ይበልጥ መስራት እንዳለባቸው ይገልጻሉ፡፡

አቶ ቢኒያም ከ80 እስከ 90 በመቶ የሚደርሰው የሳይበር ጥቃት ከአጠቃቀም ስህተት የሚከሰት መሆኑን ጠቅሰው፤ በግለሰብ ጀምሮ የጥቃት ኢላማ እንደሚሆኑ በማወቅ ጠንካራ የይለፍ ቃል መጠቀምና ከማይታወቅ ሰው አስመስለው በሚላኩ ኢ-ሜሎች ባለመታለል እራስን ብሎም ተቋማትን ከሳይበር ጥቃት መከላከል ይገባል ይላሉ፡፡

የኢንፎርሜሽን ደህንነት የማረጋገጥ ሥራ ለአንድ ተቋም የሚተው ጉዳይ ባለመሆኑ ሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ አጋርነትና ቅንጅት እንዲኖር መስራት እንደሚገባም ይጠቁማሉ፡፡

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ዳንኤል ጉታ፤ በዘርፉ በተዘጋጀ መድረክ ላይ ባቀረቡት ጥናታዊ ጽሁፍ ደግሞ ፤ እንደ ሀገር በቁልፍ መሰረተ ልማቶች ላይ የሳይበር ደህንነት ስጋቶች ከምንጊዜውም በላይ እየጨመሩ መምጣታቸውን ይገልጻሉ።

የቁልፍ መሰረተ ልማት ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን አስቀድሞ ለመከላከል የሚያስችሉ ሀገራዊ ፍላጎትንና ዓለም አቀፍ ተሞክሮን መሰረት ያደረጉ የሕግ ማሕቀፎችና የተለያዩ የአሰራር ሥርዓቶች ሊዘረጉ እንደሚገባ ይናገራሉ፡፡

በቁልፍ መሰረተ ልማቶች የሚደርሱ ጥቃቶች በሀገር ጥቅምና ደህንነት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ የሚፈጥሩ እና በአንድ ዘርፍ የማይቆሙና የመዛመት ዕድላቸው ከፍተኛ በመሆኑ ቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማቶችን ልዩ ጥበቃ ማድረግ አስፈላጊ ነው ይላሉ፡፡

የባላንጣ ሀገራትና የውስጥና የውጭ ጥፋት ኃይሎች ቁልፍ የመሰረተ ልማቶችን ዒላማ በማድረግ ጉዳት ለማድረስ ስለሚነሱ ልዩ ጥበቃ አስፈላጊ መሆኑን አቶ ዳንኤል አንስተዋል፡፡

ሀገራት ካላቸው የፋይናንስ ፣ ቴክኖሎጂና የሰው ኃይል አቅም እንዲሁም የደህንነት ስጋታቸውን ታሳቢ በማድረግ ለተለያዩ ቁልፍ መሰረተ ልማቶች ቅድሚያ ሊሰጡ እንደሚችሉ ያስረዳሉ።

በኢትዮጵያ የቁልፍ መሰረተ ልማቶችን ከማስጠበቅ አንፃር እንደሀገር የቴክኖሎጂ አጠቃቀም እድገትንና የጥቃት ስጋት መጨመርን ተከትሎ በ2004 ዓ.ም የመጀመሪያው የኢንፎርሜሽን ደህንነት ፖሊሲ የወጣ ሲሆን ፖሊሲውም የቁልፍ መሠረተ ልማትን ደህንነት ትኩረት የሰጠ ነው ይላሉ፡፡

ለቁልፍ መሰረተ ልማት ጥበቃ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት በ2016 ዓ.ም ሀገር አቀፍ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲ በሚኒስትሮች ምክር ቤት መጽደቁንም ነው የሚጠቁሙት።

በተጨማሪም ዘርፉን በሕግ ለመቆጣጠር ብሔራዊ የክፍያ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 718/2003፣መሰረታዊ የሳይበር ወንጀሎችን የሚመለከት የ1996 ወንጀል ሕግ ከአንቀፅ 706-711 እንዲሁም የቴሌኮም ማጭበርበር አዋጅ ቁጥር 761/2004 መውጣታቸውን ያነሳሉ።

አቶ ዳንኤል እንዳሉት፤ ምንም እንኳን በዘርፉ የወጡ የሕግ ማሕቀፎች ቢኖሩም ከቁልፍ መሰረተ ልማቶች የሳይበር ደህንነት ጋር ተያይዘው የሚወጡ ስታንዳርዶችንና ሥርዓቶችን ተግባራዊ ማድረግ ክፍተት፣ የሳይበር ደህንነት ፍተሻ፣ ቁጥጥርና ግምገማ አስገዳጅነት አለመኖር በጥናቱ የተገኙ አስገዳጅ ሕጎች ክፍተቶች ናቸው፡፡

በጥናቱ ላይ ከፋይናንስ ተቋማት ውጪ ቁልፍ መሰረተ ልማት ተቋማት የራሳቸውን የሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስታንዳርድ የማውጣትና የመተግበር ክፍተት፣ ፖሊሲውን በየወቅቱ የመከለስና ተግባራዊ በማድረግ በኩል ከፖሊሲና ስታንዳርድ አንፃር ክፍተቶች መለየታቸውን ይገልጻሉ፡፡

በመሆኑም በዚህም ቁልፍ መሰረተ ልማቶችን መለያ መስፈርቶችን፣ አስገዳጅ ማሕቀፎች፣ሪፖርትና መረጃ ልውውጥ፣ ኦዲት አሰራር ማሕቀፎች፣ አገልግሎት ሰጪዎች ፈቃድ ያካተተ ሁሉን አቀፍ የሆነ የሕግ ማሕቀፍ በአዋጅ ደረጃ ማዘጋጀት የሚያስፈልግ መሆኑ በጥናቱ እንደተመላከተ ይናገራሉ።

ዝርዝር ሁኔታ የያዘ የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት የመረጃ ልውውጥና የቅንጅት ሥራዎችን በሀገር ውስጥም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ በማከናወን የሳይበር ደህንነት ጥበቃን ማጠናከር እንደሚገባም ነው የጠቆሙት።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዥ አቶ ማሞ ምህረቱ በበኩላቸው፤ በሀገሪቱ የኃይል ማከፋፈያዎች፣ የባንክ ሥርዓቶች፣ የትራንስፖርት መሰረተ ልማቶች ወይም የጤና አጠባበቅ ኔትዎርኮች ላይ አንድ ጊዜ ጥቃት ከደረሰ ለማህበረሰቡ ከፍተኛ መዘዝ ሊያስከትል እንደሚችል ያመላከታሉ።

ይህም ስጋት ቴክኒካል ስጋት ብቻ ሳይሆን ጂኦፖለቲካዊ እንድምታ ያለው መሆኑን ጭምር መገንዘብ ይገባል ያሉት አቶ ማሞ፤ የሳይበር ጥቃቶች የብሔራዊ ደኅንነትን ለአደጋ የሚጋለጥ፣ ሕዝቡ በመንግሥት ላይ ያለውን አመኔታ የማሳጣትና ሀገራችን በዓለም አቀፍ መድረክ ላይ ያላትን ተጽዕኖ የመቀነስ አቅም አለው ይላሉ።

በመሆኑም የሀገሪቱን ወሳኝ መሠረተ ልማቶችን ከጥቃት ለመጠበቅ ጠንካራ የፖሊሲና የሕግ ማሕቀፎችን፣ ሀገራዊ የቴክኖሎጂ ባለቤትነትን፣ በዘርፉ ብቁና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ የሆነ የሰለጠነ የሰው ኃይል ማፍራት በእጅጉ እንደሚጠይቅ ነው የገለጹት።

# የፖለቲካ ፓርቲዎችንና...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ከተሳታፊነት ባለፈ በማማከርም ጭምር እየሰሩ መሆኑን ጠቁመው፤ በጣም ውስን የሆኑ ፓርቲዎች ደግሞ በተለያዩ ምክንያቶች በሂደቱ እየተሳተፉ አለመሆኑን አንስተዋል። ኮሚሽኑ የተቀሩት ፓርቲዎች ወደ ምክክር ሂደቱ እንዲመጡ እየሰራ ነው ብለዋል፡፡

እየተሰሩ ባሉ ስራዎች ጥሩ ውጤት መገኘቱን ያነሱት ቃልአቀባዩ፤ በዚህም በቅርቡ የተወሰኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች የምክክር ሂደቱን መቀላቀላቸውን ጠቁመዋል።

በተመሳሳይ የታጠቁ ኃይሎች ሂደቱን እንዲቀላቀሉ ጥረቶች እየተደረጉ ነው ያሉት አቶ ጥበቡ፤ እነዚህ አካላትም ወደ ምክክሩ እንዲመጡ ለማድረግ ኮሚሽኑ ብቻውን የሚሰራው ስራ ባለመሆኑ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት እየሰራ ይገኛል ሲሉ አስረድተዋል።

ኮሚሽኑ ባላው አቅም ነፍጥ ያነገቡ አካላት በሀገራዊ ምክክሩ እንዲሳተፉ በሩን ክፍት አድርጎ ለማስተናገድ ዝግጁ መሆኑን ተናግረው፤ ጥያቄያቸውን ተቀብሎ በሂደት መታየት ያለባቸውን ጉዳዮች ለማየት ያለውን ዝግጁነት በመግለጽ ጥሪ እያቀረበ ይገኛልም ብለዋል፡፡

በተጨማሪም ትጥቅ ትግል ላይ የሚገኙ ዜጎች ወደ ምክክር ሂደቱ በሚመጡበት ወቅት የሚያነሷቸው የደህንነት ስጋቶች ካሉ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በተለይም ከመንግሥት ጋር በመሆን ምቹ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ኮሚሽኑ እየሰራ መሆኑን ጠቁመዋል።

ቃል አቀባዩ እንደገለጹት፤ ኮሚሽኑ ተቋቁሞ ስራ ከጀመረ ከሁለት ዓመት በላይ ሆኖታል፤ በእነዚህ ዓመታትም በርካታ የዝግጅትና የአጀንዳ ማሰባሰብ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡

ሀገራዊ ምክክሩ ሁሉን አካታችና አሳታፊ ከማድረግ አንጻር በተሰራ ስራም ከወረዳ እስከ ዳያስፖራው ማህበረሰብ ድረስ ተሳታፊዎችን መለየት ተችሏል ብለዋል። በቀጣይም በኦሮሚያ ክልል የአጀንዳ ማሰባሰብ ስራውን ለማጠናቀቅ መታቀዱን ተናግረዋል፡፡

ኮሚሽኑ በክልሎቹ ባለው ነባራዊ ሁኔታ ኮሚሽኑ ተንቀሳቅሶ ስራውን መስራት ባለመቻሉ በአማራና ትግራይ ክልሎች ተሳታፊዎችን መለየትም ሆነ አጀንዳ የማሰባበሰብ ስራ አለማከናወኑን ተናግረዋል።

በትግራይ ክልል የምክክር ሒደቱን ለማከናወን የሚያስችሉ ውይይቶች መደረጋቸውን አስታውሰው፤ በቀጣይ ኮሚሽኑ በክልሉ ስራውን የሚጀምር ይሆናል ሲሉም ገልጸዋል፡፡

በአማራ ክልል ባሉ ግጭቶች ምክንያት ሙሉ በሙሉ ስራዎችን ማከናወን ባይቻልም ኮሚሽኑ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ተባባሪ አካላትን የመለየትና ስልጠናዎችን የመስጠት እንቅስቃሴዎችን አድርጓል ብለዋል።

እንቅስቃሴዎቹ ግን በሁሉም ወረዳዎች በተሟላ መልኩ ማካሄድ ባለመቻሉ የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት አልተቻለም ሲሉ ገልጸዋል።

በሁለት ክልሎች ያሉ ፈታኝ ሁኔታዎች እንዲስተካከሉና አንጻራዊ በሆነ ሁኔታ ስራውን እንዲሰራ ኮሚሽኑ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ጥረት እያደረገ መሆኑን ጠቁመው፤ በክልሎች ያሉ ሁኔታዎች ሲመቻች በፍጥነት ወደ ስራ መግባት የሚቻልባቸው ጉዳዮች ላይ በትኩረት እየተሰራ መሆኑንም አመላክተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ያረጀ የቅኝግዛት እሳቤ ከመራመድ ወጥቶ ለማሕቀፉ ትግበራ ተባባሪ መሆን ብልህነት ነው!

ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን ለፍትህ እና ለፍትሐዊነት ካላቸው ዘመን ተሻጋሪ ማህበረሰባዊ እሴት አኳያ፤ በናይል ውሃ አጠቃቀም ዙሪያ ፍትሐዊነት እንዲሰፍን ብርቱ ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል። ለዚህ አስተሳሰብ ባእድ የሆኑ የቅኝ ግዛት ውሎች በብዙ መስዋእትነት ነጻነቱን የተቀዳጀውን የአሁኑን አፍሪካዊ ትውልድ እንደማይመጥኑ ድምጿን ከፍ አድርጋ አሰምታለች።

ፍትሐዊነት ዓለም አቀፍ መርህ ተደርጎ በሚወሰድበት አሁናዊው ዓለም፤ እንደሀገር ስለፍትሐዊነት ያሰማቻቸው ድምጾች በዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ዘንድ ተገቢውን ጆሮ ሳያገኙ በመቅረታቸው፤ ሀገሪቱ በተለይም የዓባይ ወንዝን በፍትሐዊነት ለማልማት ያደረገችው ጥረት በብዙ ፈተናዎች የታጀበ እንዲሆን አድርጎታል።

የአንድ ሀገር ሆነ ሕዝብ የመልማት ጥያቄ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው በዓለም አቀፍ ህጎችም የተደገፈ ነው። በተለይም ባለንበት ዘመን የመልማት ጥያቄ የበለጸገች ዓለም ለመፍጠር ከሚደረገው ጥረት አኳያ በእጅጉ የሚበረታታ እና ዓለም አቀፍ እውቅና የተቸረው ነው። ሰብአዊ መብትም ተደርጎ የሚወሰድም ነው።

ሀገራችን ኢትዮጵያም በተለያዩ ወቅቶች ያሏትን የተፈጥሮ ጸጋዎች በመጠቀም ከድህነት እና ከኋላቀርነት ለመውጣት የተለያዩ ጥረቶችን ስታደርግ ቆይታለች። በተለይም የውሃ ሀብቷን በሁለንተናዊ መልኩ በመጠቀም ሕዝቦቿን ተጠቃሚ ለማድረግ ያደረገቻቸው ጥረቶች ዛሬን በማይመጥኑ የቅኝ ግዛት ውሎች ሲፈተኑ ቆይተዋል።

እነዚህ በናይል ወንዝ ውሃ አጠቃቀም ዙሪያ ቅኝ ገዥዎች ያሠሩዋቸው ውሎች የየትኛውንም አፍሪካዊ ፍላጎት ያላካተቱ፣ከዛ ይልቅ የወቅቱ ቅኝ ገዥ ሀገራትን ጥቅሞች መሰረት ያደረጉ ፣ ከነጻነት በኋላም በተፋሰሱ ሀገራት መካከል የነበረውን አፍሪካዊ ወንድማማችነትን በመቀጨጭ አለመተማመንን እየፈጠሩ የነበሩ ናቸው።

የተፋሰሱ ሀገራት በነጻነት ትግሉ ወቅት የተፈጠረውን የፓን አፍሪካኒዝም እሳቤ ፣ እሳቤው የወለደውን ወንድማማችነት ፣ ከዚህ የሚመነጭ መደጋገፍ እና አብሮ የማደግ መነሳሳት ተጨባጭ እንዳይሆን ትልቅ ተግዳሮት፤ ከዛም አልፎ በተፋሰሱ ሀገራት የመልማት ፍላጎት ላይ ትልቅ ደንቃራ ሆነዋል ።

በተለይም በተለያዩ ወቅቶች ወደ ስልጣን የመጡ የግብጽ መንግሥታት የወንዙን ውሃ ሁሌም የሀገር ውስጥ ፖለቲካ አጀንዳ አድርገው በማቅረብ፤የወንዙን ውሃ በተፋሰሱ ሀገራት መካከል የግጭት እና የአለመተማመን ምንጭ እና የሀገር ውስጥ ፖለቲካ ጊዜ መግዣ ለማድረግ ሰፊ ጥረቶችን ሲያደርጉ፤ ባልተገባ መልኩ በተደጋጋሚ ዓለም አቀፍ አጀንዳ ለማድረግም ሲሞክሩ ማየት የተለመደ ነው።

በፍትሐዊ ተጠቃሚነት መርህ ከተፋሰሱ ሀገራት ጋር አብሮ ለጋራ ተጠቃሚነት ከመሥራት ይልቅ ፤ ጊዜ ያለፈባቸውን የቅኝ ግዛት ውሎች የሙጥኝ የማለቱ የግብጽ መሪዎች የቀደመ ሆነ አሁናዊ አካሄድ፤ በየትኛውም መንገድ የግብጽን ሕዝብ ከወንዙ ውሃ የተሻለና ዘላቂ ተጠቃሚ አያደርገውም።

መንግሥታቱ እስካሁን እየሄዱበት ያለው የሴራ መንገድም ቢሆን፤ዘመኑን የማይመጥን ፣ዓለም አቀፉን የዲፕሎማሲ መንገድ የተቃረነ ፣ቀናት እየተቆጠሩ ሲሄዱ በአደባባይ ድምጽን ከፍ አድርጎ ለመናገር የሞራል ድፍረት የሚያጎናጽፉ አይደሉም። የግብጽን ሕዝብ በዓለም አቀፍ መድረክ ከማሳነስ ያለፈ ፋይዳም አይኖራቸውም።

በተለይም አሁን ላይ አብዛኞቹ የተፋሰሱ ሀገራት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ የወንዙን ውሃ ለመጠቀም ፣ የናይል ወንዝ ተፋሰስ የትብብር ማሕቀፍ ስምምነት ህጋዊ ባደረጉበት ወቅት ስለ ቅኝ ግዛት ውሎች ሙግት ለመግጠም መሞከር ፤ የግብጽ መሪዎች ዛሬም ከቅኝ ግዛት አንጎበር እንዳልወጡ የሚያመላክት ነው ።

ዓለም በሁለንተናዊ መልኩ ወደ አንድ መንደርነት እየተጓዘች ባለችበት ፤ለዚህ የሚሆን ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርግ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ መስተጋብር እየፈጠረች ባለችበት ፤አለመተማመንን እና ጠላትነትን በሚፈጥሩ ጊዜ ያለፈባቸው አስተሳሰቦች የተቃኙ የቅኝ ግዛት ውሎችን የሙጥኝ ማለት ዘመኑን የሚመጥን የፖለቲካ እሳቤ አይደለም።

የግብጽ ፖለቲከኞች ለሕዝባቸው ብሩህ ነገዎች ታማኝ ከሆኑ ፤ታማኝነታቸው ሊመነጭ የሚችለው ዛሬ ላይ ትርጉም አልባ የሆኑ ትርክቶችን ከመደጋገም ወጥተው ፤ከአፍሪካዊ ወንድሞቻቸው ጋር በሰላም እና በፍቅር፤ በመከባበር እና በመተማመን ላይ የተመሰረተ ማህበራዊ ፣ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ መስተጋብሮችን በመፍጠር የጋራ ተጠቃሚነትን ማስፈን ሲችሉ ብቻ ነው ።


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የሳይበር ደህንነትን ማስጠበቅ የጋራ ኃላፊነት ነው!

**ስሜነህ ደስታ**

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር(ኢመደአ) የሀገራችንን ቁልፍ ኢንፎርሜሽን እና የኢንፎርሜሽን መሰረተ-ልማት ደህንነትን በማረጋገጥ የሳይበር ምህዳሩን ለሀገራችን ሰላም፣ ልማትና ዲሞክራሲ መርሃ ግብሮች ማስፈፀሚያ እንዲሆን እንዲሁም የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅሞች ለማስጠበቅ በሀገር ደረጃ የተጣለበትን ኃላፊነት እየተወጣ የሚገኝ ነው፡፡

አስተዳደሩ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ላለፉት 18 ዓመታት በርካታ ወሳኝ ሀገራዊ ፕሮጀክቶች በማከናወን የኢትዮጵያን የሳይበር ምህዳር ደህንነት በማረጋገጥ፣ በቴክኖሎጂ የላቀና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆኑ ሥራዎችን በመሥራት፣ ሀገራዊ ሀብትን በመፍጠር እንዲሁም አቅም ባልተገነባባቸው የኢንፎርሜሽንና የመረጃ ቴክኖሎጂዎች ላይ አቅም በመፍጠር የሀገራችንን የሳይበር ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ ከፍተኛ ሥራዎችን እየሠራም ይገኛል፡፡

ባለፉት ዓመታት በኢትዮጵያ የሳይበር ምህዳሩን የሚጠቀመው ቁጥር መጨመርና ሳይበር የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ተጽዕኖ ማሳደሪያ እየሆነ መምጣቱን ተከትሎ በግለሰቦች፣ በመንግሥት ቁልፍ ተቋማት እና ቁልፍ መሰረተ-ልማቶች ላይ የሚሰነዘሩ የሳይበር ጥቃቶች በዚያው ልክ እንዲጨምር አድርጓል። እነዚህን ጥቃቶች ደግሞ አስተዳደሩ በተቻለው መጠን አቅሙን በመገንባት እየተከላከላቸው ይገኛል፡፡

ጥናቶች እንደሚያሳዩት በዓለም አቀፍ ደረጃም ሆነ በሀገራችን የሳይበር ጥቃቶች መነሻ በመሆን ትልቁን ድርሻ የሚይዘው ተጠቃሚዎች ስለ ሳይበር ምህዳሩ ያላቸው የግንዛቤ ደረጃ አነስተኛ ከመሆን ጋር የተያዘ ነው፡፡የተጠቃሚዎች የግንዛቤ ማነስ ለሳይበር ጥቃቶች ማደግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረጉን የተረዱ ሀገራት የጥቅምት ወርን የሳይበር ደህንነት የግንዛቤ ማስጨበጫ ወር በሚል የሚያከብሩ ሲሆን ዘንድሮም በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ21ኛ ጊዜ በመከበር ላይ ይገኛል።

በሀገራችንም በአስተዳደሩ አስተባባሪነት የጥቅምት ወር ሀገር አቀፍ የሳይበር ደህንነት ንቃተ- ህሊና ማጎልበቻ ወር በማድረግ ዘንድሮ ለአምስተኛ ጊዜ ‹‹ቁልፍ መሰረተ-ልማት ደህንነት ለዲጂታል ሉዓላዊነት›› በሚል መሪ ቃል እየተከበረ ይገኛል። ቁልፍ መሰረተ-ልማቶቻችንን ደህንነት መጠበቅ የሀገራችንን ደህንነትና ሉዓላዊነት በማረጋገጥ ረገድ የሚኖረው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡

ቁልፍ መሰረተ- ልማቶች ለአንድ ሀገር ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ መስተጋብር ዕድገት ካላቸው የማይተካ ጠቀሜታ አኳያ ጉዳት በሚደርስባቸው ወይም በሚስተጓጎሉበት ጊዜ በዜጎች የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳድራሉ፡፡ ከዚህም ባሻገር ከሳይበር ምህዳር ማግኘት የሚገባንን ብሔራዊ ጥቅም ያሳጣሉ፡፡ በአጠቃላይ ብሔራዊ ደህንነትን አደጋ ላይ ይጥላሉ፡፡ይህ እንደመሆኑም ልዩና ጠንካራ ጥበቃ ሊደረግለት የግድ ነው፡፡

የሀገራችንን ቁልፍ መሰረተ-ልማቶች ደህንነት መጠበቅ የአንድ ተቋም የተናጠል ኃላፊነት ብቻ ሳይሆን የእያንዳንዱ ዜጋ እንዲሁም የግልና የመንግሥት ተቋማት የጋራ ጥረትና ትብብርን የሚጠይቅ ጉዳይ ይሆናል፡፡ እንደ ሀገር የሳይበር የመከላከል አቅም ከፍ ለማድረግና ለማጠናከር፣ ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ መረጃን መለዋወጥ እንዲሁም በሳይበር ደህንነት ዙሪያ አዳዲስ ፈጠራዎችን መደገፍ የትብብር አካባቢን መፍጠርና በጋራ መሥራት ለነገ የሚተው ጉዳይ መሆን የለበትም፡፡

የትብብር አካባቢን በመፍጠር በጋራ ከመሥራት በተጨማሪ ተቋማት ጠንካራ የሳይበር ደህንነት ማስጠበቂያ አማራጮችንና እርምጃዎችን በመውሰድ፣ ለሠራተኞቻቸው ተገቢውን የሳይበር ደህንነት ግንዛቤ ስልጠና የሚሆን በጀት በመመደብ እንዲሁም በየጊዜው እየጨመሩ ከሚመጡ የሳይበር ጥቃቶች በመጠበቅ የሀገራችንን ወሳኝ መሰረተ-ልማቶች ደህንነት ማረጋገጥ ተገቢ የሆነ ብሔራዊ አጀንዳ ነው፡፡

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር መረጃ እንደሚያመለክተው በሀገራችን ሳይበር ደህንነት በሚመለከት የሚስተዋሉ ዘርፍ ብዙ ውስንነቶችና እሳቤዎች አሉ፡፡‹‹ጠንካራ የይለፍ ቃላትን በመጠቀም ብቻ ከሳይበር ጥቃት ራሴን መከላከል እችላለሁ››ብሎ ማመን አንደኛው ነው።ይሁንና ምንም እንኳን ጠንካራ የይለፍ ቃላትን መጠቀም የሳይበር ደህንነትን ለማስጠበቅ አንዱ የጥንቃቄ እርምጃ ቢሆንም ብቸኛው መፍትሄ ግን አይደለም፡፡ ከይለፍ ቃላት በተጨማሪ ሌሎች የሳይበር ደህንነት ጥንቃቄ እርምጃዎችንም ማወቅና መተግበር ወሳኝ ነው፡፡

‹‹የሳይበር ጥቃት አጥቂዎች ግዙፍ ድርጅቶችን እንጂ አነስተኛና መካከለኛ ድርጅቶችን ኢላማ አያደርጉም››ብሎ ማሰብም ጎልተው ከሚስተዋሉ የተሳሳተ እሳቤዎች መካከል ነው፡፡ አንድ መታወቅ ያለበት ዋነኛ ጉዳይ ቢኖር ማንኛውም ድርጅት የሳይበር ጥቃት ፈፃሚዎች ኢላማ የመሆን እድል እንዳለው ነው፡፡ለአብነት የAccenture የሳይበር ጥቃት ጥናት፣በ2024 ብቻ 43 በመቶ የሚሆኑ ጥቃቶች በአነስተኛና መካከለኛ ቢዝነስ ተቋማት ላይ መድረሱን ያመለክታል፡፡ይህን መሰል ጥናቶችም ጥቃቶቹንም ለመከላከል ሁሉም ዘወትር ዝግጁ ሊሆን የግድ እንደሚል ምስክር የሚሆኑ ናቸው፡፡

‹‹ከአንድ በላይ ፀረ ቫይረስ መጠቀም ከሳይበር ጥቃት የበለጠ ይከላከላል››ብሎ ማሰብ ሌላው የተሳሳተ እሳቤ ነው፡፡ይሁንና ቫይረሶች ከተጠቃሚው ፍቃድ ውጪ በኮምፒውተሮችና ስማርት መሳሪያዎች ሥራ ላይ ጣልቃ ሊገቡ የሚችሉና ከውጭ ሆነው በእንግዳ ፋይሎች እና ኮምፒውተሮቻችን ከገቡ በኋላ ራሳቸውን በአስተናጋጅ ፋይሎች ውስጥ ለመደበቅ የሚሞክሩ የተለያዩ ተንኮል አዘል የኮምፒዩተር ፕሮግራሞች መሆናቸውን ጠንቅቆ መረዳት ተገቢ ነው፡፡

ቫይረሶች በደረሱባቸው ኮምፒውተሮች ላይ ሊባዙ ወይም ሊሠሩ ይችላሉ። ስለዚህ የኮምፒውተር መረጃን፣ ፋይሎችን፣ የኮምፒውተር ሲስተሞችን ወይም ፕሮግራሞችን ማግኘትና ያለተጠቃሚ ፈቃድ ተንኮል አዘል ሥራዎችን ማከናወን ይችላሉ። በመሆኑም የኮምፒውተራችንን ወይም ስማርት መሳሪያዎቻችንን ደህንነት ከሚያስጠብቁልን ነገሮች መካከል ጸረ ቫይረስ አንዱ ነው፡፡የተለያዩ ከአንድ በላይ ፀረ ቫይረሶችን በአንድ ጊዜ መጠቀም ጠቃሚ ሳይሆን እርስ በራሳቸው ሥራቸውን ከማከናወን ሊተጋገዱና ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉበት ሁኔታ ስለሚፈጠር ከአንድ በላይ ፀረ ቫይረስ መጠቀም ተገቢ አይደለም፡፡

በመጨረሻ ሊታይ የሚገባውና በዋነኛነት ትኩረት ተሰጥቶት ግንዛቤ መውሰድ የሚገባው፣ ለጽሑፌም ዋና ማጠንጠኛ የሆነው የተሳሳተ እሳቤ የሳይበር ደህንነትን ማስጠበቅ የአይቲ ክፍል እና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ብቻ ነው ብሎ ማሰብ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ ያለው እውነታ፡ የሳይበር ደህንነትን ማስጠበቅ የጥቂት የሚመለከታቸው አካላት ብቻ ሳይሆን ሁሉም ሰው ሊተባበርለት የሚገባ ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ እያንዳንዱ የምህዳሩ ተጠቃሚ ሁሉ ለጥቃት ተጋላጭ ነው፡፡ ስለሆነም ጥቃቱን ለመከላከል ሁሉም ኃላፊነት እንዳለበት መረዳት ይገባዋል፡፡

በመሆኑም ግለሰብ እንደግለሰብ እንዲሁም ተቋማት በተቋማቸው ደረጃ የሳይበር ደህንነታቸውን ከማስጠበቅ አኳያ ትኩረት ሰጥተው መሥራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተለይ ተቋማት ተገቢውን የሳይበር ደህንነት አደረጃጀት እና የአሠራር ሥርዓቶችን መዘርጋት፤ ደህንነቱ የተጠበቀ ቴክኖሎጂ መታጠቅ፤ እንዲሁም የሠራተኞቻቸውን የሳይበር ደህንነት ንቃተ-ሕሊና በየወቅቱ በቀጣይነት መገንባት ይጠበቅባቸዋል። ምክንያቱም የሳይበር ደህንነትን መጠበቅ የአንድ ተቋም ወይም የመንግሥት ኃላፊነት ብቻ ሳይሆን የሁላችንም የጋራ ኃላፊነት ነው::

# ሕገ ወጥ ፍልሰትን መከላከልና የመቆጣጠሩ ተግባር "ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ" እንዳይሆን

**ታሪኩ ዘለቀ**

ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ባላት የሺህ ዓመታት ታሪክ በርካታ ፍልሰተኞች በአግባቡ የተቀበለች፣ ያስተናገደች፣ የሸኘች፣ የወደዱትም ሲኖሩ ኢትዮጵያዊ ሲሞቱ ኢትዮጵያ ሆነው የኖሩባት ድንቅና ደግ ሀገር ነች። አሁንም ድረስ ሚሊዮኖች ያስጠለለችው ይህች ሀገር፣ ባህር አቋርጠው ከሶሪያና ከየመን ጨምሮ ከጎረቤትና ከሌሎች ሀገራትም የመጡ ፍልሰተኞች ውሎ ማደሪያም ነች።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሕገ ወጥ ፍልሰት መንስኤ ከሆኑ ምክንያቶች መካከል ጦርነት፣ የኢኮኖሚ ቀውስ፣ ድህነት፣ ሥራ አጥነት፣ የሕገ ወጥ ደላሎች ቅስቀሳ፣ የቤተሰብና የጓደኛ ግፊት፣ ጥቂት ተሳክቶላቸውና ገንዘብ ይዘው የተመለሱ ሰዎችን እንደ ምሳሌ ማየት በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው።

ወጣቶችን ለሕገ ፍልሰትን ከሚገፋፉ ምክንያቶች መካከልም የግንዛቤ ማነስ፣ የሀገር ውስጥ የሥራ አማራጮችን ያለ ማየት፣ሥራን ማማረጥ፣ ኑሮን ማሻሻል የሚቻለው በስደት ብቻ ነው ብሎ ማመን፣ ሥራ አጥነትና ድህነት፣ ጎልተው ይጠቀሳሉ።

ሕገ ወጥ ፍልሰት የአንድ ሀገር ብሎም አህጉር ችግር አይደለም። በሁሉም የዓለማችን ክፍል የሚታይ ነው። ይሁንና በታዳጊ ሀገሮች በተለይ ደግሞ ከሳሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገራት ችግሩ ገዝፎ ይታያል። ኢትዮጵያም በሕገ ወጥ ፍልሰት እጅጉን ከሚፈተኑና ከሚሰቃዩ ሀገራት አንዱ ናት።

ሕገ ወጥ ፍልሰትን ምርጫ ያደረጉ በርካታ ኢትዮጵያውያም ተስፋ ያሳደሩበትን ያህል ሕይወታቸውን ሊለውጥ የሚችል ገንዘብ ሊያገኙ ቀርቶ፤ ላልተጠበቀ አደጋ እየተጋለጡ ወደማይወጡት ማህበራዊ ቀውስ ሲገቡ ማየት እጅጉን የተለመደ አሳዛኝ ትዕይንት ነው። እንደዚህ ዓይነቱ የ"አተርፍ ባይ አጉዳይ" ክፉ እጣ የሚገጥማቸውን ኢትዮጵያውን ቤት ይቁጠራቸው ሲሉ የዓይን ምስክርነት የሚሰጡ ወገኖች ጥቂቶች አይደሉም። ቢያንስ ሰብዓዊ መብታቸው እንኳ ሳይከበርላቸው በመከራ የሚሞቱ ደማቸውም ደመ ከልብ ሆኖ የሚቀሩ ሺህዎች ናቸው።

ይህንን መመስከር የሚችሉት ቀይ ባህር፣ ሜዲትራኒያን፣ የሊቢያ በረሀዎች፤ የሱማሊያ፣ የጅቡቲ፣ የየመንና የሳውዲ አሸዋዎች፤ የታንዛኒያና የማላዊ ጫካዎችና ዋሻዎች ብቻ ናቸው። በሀገራቸው ቢሰሩ የሚለወጡበትን ገንዘብ ለደም መጣጮች አውሬ ደላሎችና በሕገ ወጥ ለደለቡ አሳሞች አስረክበው ሥጋቸውንም ነፍሳቸውንም ሸጠው በሞት ሸለቆ ውስጥ አልፈው ወደ ሲኦል ይጓዛሉ።

በሰላም ደረሱ የሚባሉት እንኳ ትንሽ የሰሯትን የደቡብ አፍሪካ ወሮበላ እና የአረብ ፖሊስ ዘርፏቸው ባዶ እጃቸውን ወጥተው ለአካልም ለአእምሮ ህመም የሚጋለጡት የትየሌሌ ናቸው። የቀሩትም እየታፈሱ እንኳን የሰው ልጅ አውሬ እንኳ በማይኖርበት ጭካኔ እጅግ አሰቃቂ ምድራዊ ሲኦልን እንዲኖሩ ይገደዳሉ።

ሁሉም ከቤቱ ሲወጣ ብዙዎቹን በበርሃ በአሸዋ የተዋጡትን፣ በባህር ሰምጠው የቀሩትን ሳይሆን ካዛ መህል አሰቃቂውን መንገድ አልፈው የተሻለ ኑሮ ያገኙትን ጥቂቶቹን አይቶ እነሱን ሊሆን ተመኝቶ ነው። በዚህ የተሻለ ሕይወትን ፍለጋ በሚደረግ ሕገ ወጥ ስደት ለቁጥር የሚዳግቱ ኢትዮጵያዊያን በአሰቃቂ ሁኔታ ባህር አሰምጧቸው፣ አውሬ በልቷቸው፣ ሰው ጎድቷቸው ምኞታቸውን ሳያሳኩ ሞት ወስዷቸዋል።

ይህ የብዙ ኢትዮጵያዊያን የጋራ የሰቆቃ ታሪክ ነው። ዛሬም ይህ ሲቃይ መቆሚያ አላገኘም። ዛሬም ኢትዮጵያዊያን ከአካላዊና ሥነ ልቡናዊ ጉዳት አልፈው የበረሀው አውሬና የባህር አሳ ነባሪ ሲሳይ እየሆኑ ነው። በቅጡ እንኳን ስለሞታቸው ያልተነገረላቸው ዜጎችን ቁጥር ቤት ይቁጠራቸው።

እውነታው ይህ ቢሆንም ችግሩን በቅጡ ተረድቶ ከሕገ ወጥ ፍልሰት ራሱን የሚገታ ኢትዮጵያዊ ቁጥር ትንሽ ነው ለማለት ያስደፍራል። ችግሩ ለበርካታ ዓመታት አብሮን ኖሮ ሺህዎች ወንድም እህቶቻችንን ሕይወት ቢነጥቅም አሁንም የሕገ ወጥ ደላሎችን በመከተል ወደ ሞት የሚሄደው ዜጋ ቁጥር በርካታ ነው።

ለዓመታት በዜጎች ላይ ከታየውና ከደረሰው አደጋ ይልቅ ለማይጨበጥና በአጉል ምኞት ለሚያናውዙ ሕገ ወጥ ደላሎች ቀልቡን የሰጠው ብዙ ሆኗል። ለዜጎች አይደለም ለሰው ልጅ ደንታ የሌላቸው፣ በሰው ላብና ደም፣ ሀብትና ንብረት ማካበት የዓለም መጨረሻቸው ያደረጉ ሕገ ወጥ ደላሎች ሃሳብና አካሄድ የሁሉንም ቀልብ በሚስብ መልኩ ነው።

በተለይ በድህነት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ደላሎች በሚሰጡት የሀሰት ተስፋና መደለያ የመሳሳት እድላቸው የሰፋ ነው። ይህ በመሆኑም ሕገ ወጥ አዘዋዋሪዎች በድህነት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችንና ለስደት የተለየ አመለካከት ያለበት አካባቢን ኢላማ አድርገው ይንቀሳቀሳሉ። የዘርፉ ምሁራን እንደሚገልፁት በተለምዶ ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር የሚባለው በሰው መነገድና ሰውን በሕገ ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀል ችግሮችን ያጠቃልላል።

ይህ በተደራጁ ወንበዴዎች የሚፈፀም ሕገ ወጥ ተግባር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየረቀቀ መጥቷል። ኢትዮጵያዊያንም የዚህ ከሀገር ውስጥ እስከ ዓለም አቀፍ ትስስር ያለው ወንጀል ሰለባ መሆናቸውን ቀጥለዋል። በሂደቱ በርካቶች እድል ከእነሱ ጋር ሆና ነፍሳቸውን ይዘው ተመልሰው ዛሬ ያለፉበት ስቃይ እያመማቸውም ቢሆን እንደ ታሪክ ለማውራት የበቁ አሉ። ሕይወት ይህንን ሁለተኛ እድል ያልሰጠቻቸው በቁጥር ይበዛሉ። በየጊዜው የሚሰማው ለጆሮ የሚከብድ የስደተኞች የሞት ዜናንም እየተላመድነው ያለ ክፉ የታሪክ ገጽ ሆኗል።

በይበልጥ ባለፉት ዓመታት ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር የሚፈጥረው ስቃይ በዛ ብሎ እያየን ነው። መዳረሻቸውን አውሮፓና ደቡብ አፍሪካ አድርገው ከሀገራቸው የሚነሱ ኢትዮጵያዊያንም በሊቢያና በሌሎችም ሀገራት ስቃይ ላይ ሆነው ፎቶ እየተላከ ከፍተኛ ማህበረሰባዊ ቀውስ ሲፈጥር እያየን ነው።

በርግጥ መንግሥት ችግሩን እስከ ወዲያኛው ለመቅረፍ የሚያደርገውን ተግባራዊ እንቅስቃሴ ከጀመረ ውሎ አድሯል። በሀገርና በዜጎች ላይ ከፉ ጠባሳ እያስቀመጠ የሚገኘውን ይህን ዓለም አቀፍ ችግር ለመፍታት ጥረቶቹ እንደቀጠሉ ናቸው። ችግሩ እንደ ሀገር እያስከተለ ያለውን ቀውስ መንግሥት በአግባቡ ተገንዝቦ የተለያዩ ተግባራትን ከውኗል። ከክውኖቹ መካከል የሕግ ማዕቀፎችን ማዘጋጀትና ዜጎችን ወደ ሀገራቸው መመለስ ተጠቃሽ ናቸው።

በሰው መነገድና ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ሰውን ድንበር ማሻገር ወይም በአጠቃላይ ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተለያዩ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች አሉ። የመጀመሪያው የተደራጁና ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ ስምምነት ነው። ይህንን ስምምነት ተከትሎም ሁለት አጋዥ ፕሮቶኮሎች ወጥተዋል። እነዚህን ፕሮቶኮሎች ኢትዮጵያ ተቀብላ የሕግ አካል አድርጋለች።

ይህ ብቻ ሳይሆን እነዚህን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ወደ መሬት ለማውረድ በሀገር አቀፍ ደረጃ በሰው መነገድና ሰውን ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር አላማ አዋጅ ቁጥር 1178/2012 እንዲወጣ ተደርጎ ወደ ሥራ ተገብቷል። ይህ አዋጅ በ2012 ዓ.ም የወጣ ነው። አዋጁ ከወጣ ጀምሮ ወንጀሎችን ከመከላከል ጀምሮ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ተሰርተዋል።

ወንጀሎቹ ተፈፅመው ሲገኙ ከመመርመር፣ ከመክሰስ፣ ከማስቀጣት፣ ተጎጂዎችን ከመጠበቅ አንፃር እና በሀገር አቀፍም፣ በዓለም አቀፍም የተለያዩ ሥራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ። ይህንን አላማ ለማሳካትም የተለያዩ አደረጃጀቶች ተፈጥረዋል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ወንጀል ለአዘዋዋሪዎቹ አትራፊ ከሚባሉ የወንጀል ዓይነቶች አንዱ ነው። በዚህ ሂደት ውስጥ የሚሳተፉ ወንጀለኞች አቅምም ፈርጣማ ነው። ይህ ወንጀል በባህሪው ከማህበረሰቡ ጀምሮ የብዙ ባለድርሻ አካላትን ትብብርና አስተዋጽኦ ይጠይቃል። ስለዚህ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ፈርጣማ የሆነ መረጃ፣ትብብርና ቅንጅት ይፈልጋል።

በመንግሥት ደረጃ በአዋጅ ቁጥር 1178/2012 መሰረት በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር የሚመራ ብሔራዊ የፍልሰት ምክር ቤት አለ። ክልሎችና የተለያዩ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት በአባላትነት የሚሳተፉበት አደረጃጀት አለ። ከዚህ አደረጃጀት በታች በፍትህ ሚኒስቴር የሚመራ ብሔራዊ የፍልሰት የትብብር ጥምረት አለ። ከትብብር ጥምረቱ በታች ስድስት የሥራ ቡድኖች ተደራጅተዋል።

አንደኛው የግንዛቤ ፈጠራ ሥራ የሚሰራ ሲሆን በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚመራ ነው። ሁለተኛው ወንጀሎችን ከመከላከልና ከሕግ ማስከበር አንፃር የተደራጀ ሲሆን ከደህንነት ተቋም ጀምሮ ብሔራዊ ባንክ፣ ኢሚግሬሽን፣ጠቅላይ ዓቃቢ ሕግ እና ሌሎች ሕግ አስከባሪ ተቋማት በአባላትነት የሚሳተፉበት የሥራ ቡድን ነው።

በተለይ ከሥራ እድል ፈጠራና ተጎጂዎችን ከመጠበቅ አንፃር ደግሞ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የሚያስተባብረው የሥራ ቡድን ተዋቅሯል። የክፍተት መረጃ አስተዳደር የሥራ ቡድን ደግሞ በኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት የሚመራ ሌላኛው ክፍል ነው። እንዲሁም ከፍልሰት ምርምር አንፃር ትምህርት ሚኒስቴር የሚመራው የሥራ ቡድን አለ። ዲያስፖራውን የሚያስተባብርም የሥራ ቡድን አለ። እነዚህ የሥራ ቡድኖች የተለያዩ አባላትን በሥራቸው አቅፈው በተለያዩ ጊዜ እቅዶችን እያቀዱ ሥራዎችን እየፈፀሙ እና እየገመገሙ በሀገር አቀፍ ደረጃ እየሰሩ ይገኛሉ። ነገር ግን ችግሩን ለመፍታት ዋናው የማህበረሰቡ ተሳትፎ ትልቅ ሚና ይኖረዋል።

መንግሥትም ሕዝባዊ ግዴታ አለበትና በየዓመቱ ሚሊዮን ገንዘብ እየከሰከሰ ቢመልሳቸውም እነሱም ሚሊዮኖችን እየከፈሉ ወደ ሞት ደጋግመው ይጓዛሉ። በዚህ ረገድ የአውሬዎቹ ደላሎች እና ለአንዳንድ ተባባሪዎቻቸው ባለሥልጣናቱ ጭካኔና ስግብግብነት እጅግ የበዛ ነውና መንግሥት ወደ ውሃ ቅዳ፣ ውሃ መልስ አድካሚና አክሳሪ ሥራ ሳይገባ በፊት በሕገ ወጦቹ ላይ የማያዳግም ርምጃ መውሰድን ማስቀደም አለበት።

ከተቀባይ ሀገራት ጋር በስምምነት የሚፈፀም ሕጋዊ አሰራርንም ማጠናከር እንደዚሁ ይገባዋል። መንግሥት ዛሬ የሚመልሳቸው ፍልሰተኞች ነገ ላለመመለሳቸው ዛሬ ላይ ርግጠኛ መሆን አለበት። ለዚህም የሚሆን ጠንካራ አሰራር እና የቁጥጥር ሥርዓት መፍጠር ይጠበቅበታል። በሕገ ወጦች ላይ የሚወሰደው ርምጃም ችግሩን በሚመጥን መልኩ ሊቀመርና ተፈፃሚ ሊሆን ይገባል።

እውነታው ይህ ቢሆንም ችግሩን በቅጡ ተረድቶ ከሕገ ወጥ ፍልሰት ራሱን የሚገታ ኢትዮጵያዊ ቁጥር ትንሽ ነው ለማለት ያስደፍራል። ችግሩ ለበርካታ ዓመታት አብሮን ኖሮ ሺህዎች ወንድም እህቶቻችንን ሕይወት ቢነጥቅም አሁንም የሕገ ወጥ ደላሎችን በመከተል ወደ ሞት የሚሄደው ዜጋ ቁጥር በርካታ ነው

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# እምርታ እያስመዘገበ ያለው የኦሮሚያ ክልል ግብርና ልማት

ማህሌት አብዱል

ኢትዮጵያ ባለፉት ዓመታት የግብርና ዘርፉን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥታ እየሰራች ትገኛለች። በተለይም የዜጎቿን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ፤ ዘርፉ የሚያስገኘውን የውጭ ምንዛሬ ገቢ ለማሳደግ ትኩረት ሰጥታ ስትሰራ ቆይታለች። በዚህም ምርትና ምርታማነት እያሳደገች መጥታለች።

ለእዚህ ምርትና ምርታማነት እድገት አስተዋጽኦ ካደረጉት መካከል የኩታ ገጠም እርሻ መስፋፋት አንዱ መሆኑ ይጠቀሳል። የዚህ የኩታ ገጠም እርሻ አስፈላጊነት የእርሻ ሥራውን በሜካናይዜሽን የታገዘ ማድረግ እንደመሆኑ እርሻው በሜካናይዜሽን እንዲታገዝ ማድረግ ከተጀመረ ወዲህ በግብርናው ዘርፍ ተጨባጭ ውጤት ማስመዝገብ ችላለች።

በግብርናው ዘርፍ ከፍተኛ እምርታ ካሳዩ ክልሎች መካከል ደግሞ የኦሮሚያ ክልል አንዱ ነው። የክልሉ መንግሥት ለግብርና ዘርፉ በሰጠው ልዩ ትኩረት በየዓመቱ የሚታረሰው መሬትም ሆነ የሚለማው የሰብል ዓይነት በከፍተኛ ደረጃ ጨምሯል። በዋናነትም ኩታ ገጠም እርሻ እንዲስፋፋ በመደረጉ የአርሶ አደሩ ምርታማነት እየጎለበተ መጥቷል።

የኦሮሚያ ግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ጌቱ ገመቹ በቅርቡ የ2016/17 የምርት ዘመን የክልሉን የግብርናው ዘርፍ እቅድ አፈፃፀም ያለበትን ሁኔታ አስመልክተው በሰጡት መግለጫ እንደገለፁት፤ በክልሉ በምርት ዘመኑ ከየትኛውም ጊዜ በላቀ ምርታማነትን ለማሳደግ ሰፊ እንቅስቃሴ ተደርጓል። "ከተረጂነት ወደ ምርታማነት" የሚለውን ሀገራዊ አቅጣጫ በመከተል በዘንድሮው የመኸር እርሻ በመሬት ሽፋንም ሆነ በምርት ከፍተኛ ለውጥ ለማምጣት እየተሰራ ነው። በተለይም በመኸር እርሻ በክልሉ 10 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በዘር ለመሸፈን ታቅዶ ሰፊ እንቅስቃሴ የተደረገ ሲሆን፣ 11 ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በተለያዩ አዝዕርት ዓይነቶች ዘር በመሸፈን ከእቅድ በላይ መፈፀም ተችሏል። ይህም ካለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር የ16 ነጥብ ሰባት በመቶ ብልጫ አለው።

«ለእቅዳችን መሳካትም በተለይም ደግሞ ኢኒሼቲቮች ላይ ከፍተኛ የሆነ ትኩረት ሰጥተን መሥራታችን የላቀ አስተዋፅኦ አበርክቷል» የሚሉት ኃላፊው፤ በእርሻውም ሆነ በእንስሳት እርባታ ዘርፍ በክላስተር በመሥራቱ ከፍተኛ ውጤት እየተገኘ ስለመሆኑ ያስረዳሉ። «ከዚህ አኳያ ዘንድሮ በምርት እንሸፍናለን ብለን ካቀድነው ውስጥ ስምንት ሚሊዮን 651 ሺ ሄክታር የሚሆነውን መሬት በክላስተር በመሸፈን ከእቅድ በላይ አሳክተናል» በማለትም ተናግረዋል። ይህም አጠቃላይ በምርት ከተሸፈነው መሬት 78 በመቶ የሚሆነውን በክላስተር መሸፈን እንዳስቻለ ያስገነዝባሉ።

የኩታ ገጠም እርሻ መስፋፋቱ ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር እንደሚያደርግ ያለፉት ዓመታት የክልሉ ተሞክሮ እንደሚያሳይ ተናግረው፤ «ምክንያቱም ደግሞ በክላስተር የተሰሩ እርሻዎች የቴክኖሎጂ፣ ምርጥ ዘርና ማዳበሪያ አጠቃቀማቸው የተሻለ በመሆኑ ምርታማነትም በዚያው ልክ የሚጨምር በመሆኑ ነው» ሲሉ ያስረዳሉ።

ዘንድሮም 78 በመቶ የሚሆነው መሬት በክላስተር በመታረሱ ምርታማነቱ የተሻለ ይሆናል ተብሎ እንደሚጠበቅ ያመለክታሉ። በምርት ዘመኑ በክልሉ 337 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት ታቅዶ እየተሰራ መሆኑን ጠቅሰው፣ ከመቼውም ጊዜ በተሻለ በሁሉም ዞኖች ላይ ከፍተኛ ዝናብ በመጣሉና አርሶ አደሩም ከፍተኛ ርብርብ በማድረጉ እቅዱ ሊሳካ እንደሚችል ነባራዊ ሁኔታው እንደሚያሳይ አቶ ጌቱ ይጠቁማሉ። ተባይና አረምን የመከላከሉ ሥራም በባለሙያ እየተመራ በመሰራት ላይ እንደሚገኝ አስታውቀዋል።

«እነዚህን ሥራዎች ስናከናውንም በዋናነት የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ሰፊ እንቅስቃሴ አድርገናል» ያሉት ኃላፊው፤ ለዚህም ቅድሚያ ሊያገኙ የሚገባቸው የእህል ዓይነቶች ላይ ከፍተኛ ትኩረት መሰጠቱን ያስረዳሉ። በተጨማሪም ከውጭ የሚገቡትን ምርቶች በሀገር ውስጥ ለመተካት እንደ ክልል እየተሰራ ስለመሆኑም ጠቅሰዋል። ወደ ውጭ የሚላከውንም ምርት ለመጨመርና በዘርፉ የሥራ እድል ለመፍጠር ርብርብ እየተደረገ መሆኑም ያስገነዝባሉ።

የምግብ ዋስትናን የሚያረጋግጡ ተብለው



አቶ ጌቱ ገመቹ



በኢኒሼቲቭ ከተለዩ ሰብሎች አንዱ በቆሎ መሆኑን አቶ ጌቱ ጠቅሰው፤ «በክልላችን የበቆሎን ምርት በከፍተኛ ደረጃ ለማሳደግ ሰፊ እንቅስቃሴ አድርገናል፤ በዚህም አንድ ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በበቆሎ እንሸፍናለን ብለን አቅደን ሁለት ሚሊዮን ሄክታር መሬት መሸፈን ችለናል» ሲሉ አብራርተዋል። በተመሳሳይም በኢኒሼቲቩ የክልሉን የዘንጋዳ ምርት ለመጨመር ትኩረት መደረጉን ይጠቁማሉ። በተለይም ቆላማና ዝናብ አጠር በሆኑ አካባቢዎች ላይ የውሃ እጥረትን ሊቋቋሙና ቶሎ ሊደርሱ የሚችሉ የዘንጋዳ ዝርያዎችን በመለየት አንድ ሚሊዮን ሄክታር በእነዚህ ዝርያዎች ለመሸፈን ታቀዶ አንድ ነጥብ 40 ሚሊየን ሄክታር መሬት በዘንጋዳ ዘርፍ የሸፈንበት ሁኔታ መኖሩን ያስረዳሉ።

እንደ እርሳቸው ማብራሪያ፤ ከውጭ የሚገቡትን የግብርና ምርቶች በሀገር ውስጥ ለመተካት ከተለዩ ሰብሎች መካከል ስንዴ ዋነኛው ነው። በዚህ መሰረት ባለፈው የምርት ዘመን በክልሉ በተለይም በበጋ መስኖ ሁለት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን የሚሆነውን ሄክታር መሬት በስንዴ ዘር እንዲሸፈን ተደርጓል። ይህንን እምርታ በማየትም በ2016/17 መኸር ወቅት 3 ነጥብ 1 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በስንዴ ለመሸፈን ታቅዶ ሦስት ሚሊዮን 165 ሺ ሄክታር መሬት ማልማት ተችሏል።

በሌላ በኩልም ኢትዮጵያ የቢራ ገብስ ከውጭ ሀገራት ታስገባ እንደነበር አስታውሰው፤ ካለፉት አራት ዓመታት ወዲህ ግን በሀገር ውስጥ አቅም ለማምረት ታቅዶ የተጀመረው ሥራ ውጤት እያመጣ መሆኑን ይናገራሉ። በተለይም የኦሮሚያ ክልል ሥነ-ምህዳር የቢራ ገብስን በስፋት ለማምረት የሚያስችል መሆኑን ጠቅሰው፣ ይህንን ማዕከል ያደረገ ሥራ መሰራቱንም ገልጸዋል። «ዘንድሮ 500 ሺ ሄክታር መሬት ላይ የቢራ ገብስ እንዘራለን ብለን አቅደን 528 ሺ ሄክታር መሬት ላይ የቢራ ገብስ መዝራት ችለናል። በአሁኑ ወቅትም ሰብሉ በጥሩ አቋም ላይ ይገኛል» ብለዋል።

በተመሳሳይ ከውጭ የሚገባውንም ሩዝ በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት የክልሉ መንግሥት ትኩረት ከሰጠባቸው ሥራዎች አንዱ መሆኑን ያስረዳሉ። ለዚህም ይረዳ ዘንድ በአማራ ክልል ፎገራ እየለማ ካለው የሩዝ እርሻ ተሞክሮ መወሰዱን ያስገነዝባሉ። «በዚህ መነሻም ዘንድሮ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን የሚሆነውን መሬት በሩዝ ለመሸፈን አቅደን ስንሰራ ቆይተን አንድ ሚሊዮን 918 ሺ ሄክታር መሬት ማልማት ችለናል» በማለት ይገልፃሉ።

እንደ አቶ ጌቱ ማብራሪያ፤ የክልሉ መንግሥት ከውጭ የሚገቡትን ሰብሎች በሀገር ውስጥ ለመተካት ከያዛቸው የዘይት እህሎች መካከል አኩሪ አተር አንዱና ዋነኛው ነው። ዘንድሮም 600 ሺ ሄክታር መሬት በአኩሪ አተር ለመሸፈን ታቅዶ 603 ሺ ሄክታር ለምቷል። በተጨማሪም ከዚህ ቀደም እምብዛም ትኩረት ተሰጥቶ ያልነበረውን የለውዝ ሰብል ለማስፋፋት ርብርብ ተደርጓል። በዚህም 500 ሺ ሄክታር መሬት ለማልማት ታቅዶ 518 ሺ ሄክታር የሚሆነውን መሬት በለውዝ ዘር በመሸፈን ከእቅድ በላይ ማሳካት ተችሏል። በተመሳሳይ 200 ሺ ሄክታር መሬት ላይ ሱፍ ለማልማት ታቅዶ 180 ሺ ሄክታር መሬት ተሸፍኗል።

«ከዚህ ባሻገር ወደ ውጭ በሚላኩ ሰብሎች ላይ በዚሁ መጠን ሰፋፊ ሥራዎች ስንሰራ ነበር» የሚሉት አቶ ጌቱ፤ ከዚህም ውስጥ ቦሎቄ ትልቁን ስፍራ እንደሚይዝ፤ ይህም የሆነው በውጭ ሀገራት ገበያ በስፋት ተፈላጊ በመሆኑ እንደሆነ ያስረዳሉ። በዚህ መሰረትም የክልሉ መንግሥት ዘንድሮ አንድ ሚሊዮን በሚሆን ሄክታር መሬት ላይ ቦሎቄ ለመዝራት አቅዶ፣ በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች እንቅስቃሴ ማድረጉንና አንድ ሚሊዮን 81 ሺ ሄክታር መሬት ማልማት መቻሉን ያመለክታሉ። «በዚሁ ልክ በተለይም ወደ ቆላማው አካባቢ 500 ሺ ሄክታር መሬት በሰሊጥ እንሸፍናለን፤ 300 ሺ 112 ሄክታር መሬት በማሾ ለመሸፈን እየሰራን ነው» ሲሉም ያብራራሉ።

እንደ ኃላፊው ገለፃ፤ የክልሉ መንግሥት በምርት ዘመኑ በኢኒሼቲቭ የያዛቸውን የልማት ግቦች ለማሳካት ያስቸለው ዘንድ የግብዓት አቅርቦት ችግርን በዘላቂነት ለመፍታት ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ ተንቀሳቅሷል። ከፌዴራል መንግሥትና ግብርና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ለግብርና ልማቱ ወሳኝ የተባሉ ግብዓቶች በወቅቱ ተደራሽ እንዲሆኑ የተቀናጀ ጥረት አድርጓል። በዋናነትም የኬሚካል ማዳበሪያ በአፋጣኝ ከውጭ ሀገር ተገዝቶ ለአርሶ አደሮቻችን በመቅረቡ የልማት ሥራውን በወቅቱ ለመጀመር ተችሏል። እንደ ክልልም የኬሚካል ማዳበሪያም ሆነ የተፈጥሮ ማዳበሪያ /ኮምፖስት/ በማምረት ለአርሶ አደሮቹ ለማቅረብ ሰፊ እንቅስቃሴ ተደርጓል።

በዚህ መሠረትም ስምንት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ኩንታል የሚሆን ኬሚካል ማዳበሪያ ለስምንት ነጥብ 64 ሚሊዮን አርሶ አደሮች ማድረስ መቻሉን ያመለክታሉ። ይህም ካለፉት ዓመታት አፈፃፀም ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ እምርታ የታየበት መሆኑንም ያስረዳሉ። «የቀረበውን ማዳበሪያ ደግሞ በትክክልም አርሶ አደሮቻችንን የማዳበሪያ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ተሰርቷል፤ በኤሌክትሮኒክ ሲስተም ለአርሶ አደሮቻችን ሥርጭቱ እንዲካሄድ ያደረግንባቸው ሁኔታዎችም አሉ። በእዚህም ከዚህም በፊት ሥርጭት ላይ የነበሩት ጉድለቶች በዚህ የምርት ዘመን እንዲፈቱ ተደርጓል» ይላሉ።

በሌላ በኩል በእንስሳቱ ዘርፍ ላይም ምርታማነት እንዲጨምር ሰፊ እንቅስቃሴ መደረጉን አቶ ጌቱ አመልክተዋል። «በተለይም በሰው ሠራሽ ዘዴ የማዳቀል ሥራዎች ከጀመርን ወዲህ ትልልቅ ውጤቶችን ማገኘት ተችሏል፤ በዘንድሮ የምርት ዘመን ደግሞ አንድ ነጥብ ስምንት ሚሊዮን የሚሆኑ ጊደሮችና ላሞችን በሰው ሠራሽ የማዳቀል ዘዴ ማዳቀል ችለናል» ሲሉም ይጠቅሳሉ።

በዶሮ እርባታ ረገድም የአንድ ቀን ጫጩቶችን በማቅረብ ሥራ ላይ ትኩረት ተደርጎ መሰራቱን ይጠቅሳሉ። በዚህም መሠረት በምርት ዘመኑ 53 ሚሊዮን የሚሆኑት የአንድ ቀን ጫጩቶች ለአርሶ አደሮች ለማድረስ መቻሉን ያስረዳሉ። በተጨማሪም ዘመናዊ ቀፎ ለአርሶ አደሩ ተደራሽ በማድረግ የክልሉን የማር ምርት በመጠንም ሆነ በጥራት ለማሳደግ ርብርብ መደረጉን ያመለክታሉ። «በምርት ዘመኑ አንድ ሚሊዮን 31 ሺ ዘመናዊ ቀፎዎችን በማሰራጨት አርሶ አደሮቻችን ተጠቃሚ ማድረግ ችለናል» ይላሉ።

በምርት ዘመኑ ትልቅ ትኩረት ከተሰጣቸው ሥራዎች አንዱ የቡና ልማቱን በከፍተኛ ደረጃ ማስፋፋት እንደሆነም ይናገራሉ። «በተለይም በቡና ችግኝ ዝግጅት ላይ በ2016 ክረምት በከፍተኛ ደረጃ ተረባርበናል፤ በዚህም ሁለት ነጥብ አምስት ቢሊዮን የቡና ችግኞችን በማዘጋጀት ለአርሶ አደሩ እንዲሰራጩና እንዲተከሉ ተደርጓል» በማለት ያስረዳሉ። የተተከሉት የቡና ችግኞች ፍሬያማ እንዲሆኑ አስፈላጊውን የባለሙያና የቴክኖሎጂ ድጋፍ እየተደረገላቸው መሆኑን ያመለክታሉ።

በተመሳሳይ እንደ ክልልም ሆነ እንደ ሀገር የሻይ ቅጠል ልማት እምብዛም ትኩረት ሳይሰጠው መቆየቱን አስታውሰው፤ «ዘንድሮ በተለየ መልኩ 413 ሚሊዮን የሻይ ቅጠል ችግኞች አዘጋጅተን በ30 ሺ ሄክታር መሬት ላይ ለመትከል አቅደን እየሰራን ነው» ሲሉም ይገልፃሉ። ከዚህ እቅድ በመነሳትም ባለፈው ክረምት 58 ሚሊዮን ችግኞች በአራት ሺ ሄክታር መሬት ላይ ለመትከል መቻሉን ያስገነዝባሉ። ይህም የክልሉን ብቻ ሳይሆን እንደ ሀገርም ያለውን የሻይ ቅጠል ማሳ መጠን በከፍተኛ ደረጃ የሚያሳድገው መሆኑን ይጠቁማሉ። በቀጣይም የክልሉ ግብርና ቢሮ በበጀት ዓመቱ በሻይ ልማት የተያዘውን ግብ ለማሳካት ርብርብ እንደሚያደርግ አስታውቀዋል።

እንደ አቶ ጌቱ ማብራሪያ፤ በምርት ዘመኑ ለተፈጥሮ ሀብት ልማት ሥራም ትልቅ ትኩረት ከተሰጠባቸው የልማት ሥራዎች ዋነኛው ነው። እንደ ሀገርም እየተተገበረ ያለው የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር ከግቡ እንዲደርስ የተቀናጀ ጥረት ተደርጓል። በተለይም ደግሞ የአንድ ቀን የችግኝ ተከላ ከፍተኛ ስኬት የተገኘበት ሲሆን፣ ከዚህ አንፃር ባለፈው ክረምት አምስት ነጥብ አንድ ቢሊዮን ችግኞችን በአንድ ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ በመትከል ውጤታማ ሥራ ተሰርቷል። የችግኞች የጽደቀት ሁኔታን በተመለከተም ሲያብራሩ፣ እስከ አሁን ባለው ሁኔታ የጽድቀት መጠኑ ወደ 92 በመቶ ደረጃ ላይ መድረሱን መረጃችን ዋቢ አድርገው ገልጸዋል።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ እንደ አጠቃላይ በምርት ዘመኑ በክልሉ የተከናወኑ ሥራዎች ከፍተኛ እምርታ የታየባቸው ሲሆኑ፣ ምርቱ ተሰብስቦ ወደ ጎተራ እስከሚገባ ድረስ አስፈላጊው ክትትልና ድጋፍ የሚደረግ ይሆናል።

ማህበራዊ

# አስኳላ

# የመጪው ዘመን የስፔስ ሳይንስ ባለሚሎች

ግርማ መንግሥቴ

በትምህርት ዓለም ያለፈ ሁሉ ስለ "ሳይንስ" ትምህርት ሲነሳ ሁሉም የየራሱ የሆኑ ትዝታዎች አሉት። ትዝታዎቹ ምንም ይሁኑ ምን ግን ምንጫቸውም ሆነ ምክንያታቸው ሳይንስን ከመጥላት የመነጨ እንደማይሆን በርግጠኝነት መናገር ይቻላል። በተለይ በአሁኑ፣ በዚህ ሳይንስ ገላጮችን ጨምሮ "ኧርዝ ሳይንስ"፣ "ማቴሪያል ሳይንስ"፣ "ኮምፒውተር ሳይንስ" ወዘተ የመሳሰሉት ለአደባባይ ከበቁና የትምህርት አምባን ከተቀላቀሉ በኋላ የተማሪዎች ፍላጎት በዚያው ልክ ሰፍቶ ወደ ተወዳዳሪነቱ ዓለም እስኪመጡ ድረስ ገፋፍቷቸው እንመለከታለን።

በተለይ በትምህርት ተቋማት ውስጥ የተጓዳኝ ትምህርት ተገቢውን የክብር ቦታ አግኝቶ በነበረባቸው ዓመታት ክበባትና የተማሪዎች የክበባት ተሳትፎ ምን ያህል ብቁ ዜጎችን አፍርቶ እንደነበር የሚዘነጋ አይደለም። አሁንም፣ የተቀዛቀዘው ተጓዳኝ ትምህርት ዳግም ነፍስ ይዘራ ዘንድ የሚመለከታቸው ሁሉ አምርረው ሊንቀሳቀሱ ይገባል።

ከላይ እንደዘረዘርናቸው ሁሉ፣ "ስፔስ ሳይንስ"ንም ከተመለከትን ከስምና ሥያሜው ጀምሮ ደስ ይላል፤ ቀልብን ይስባል። በተለይ በወጣትነትና ተማሪነት እድሜ ወደፊት የሳይንስ፣ በተለይም የስፔስ ሳይንስ ሰው "ለመሆን የማይመኝ የለም" ማለት እስኪቻል ድረስ የጥናት መስኩ ያጓጓል። ጉጉት ብቻ ሆኖ እንዳይቀር ከተሰራ ደግሞ መሆን የማይቻልበት ምንም ዓይነት ምክንያት የለምና መሆን የፈለጉ ሆነው እያየናቸው ነው።

በዘንድሮው ዓለም አቀፍ የአስትሮኖሚ ኦሎምፒያድ ውድድር ኢትዮጵያን በመወከል የተሳተፉትና ሀገራቸውን ያስጠሩት የዛሬው እንግዳችን ተማሪ ፍትሕ ግርማ (የብር ሜዳሊያ)፣ ተማሪ ሚካኤል አሸናፊ እና ተማሪ አላዛር አዳነ (እያንዳንዳቸው የነሐስ ሜዳሊያ)፣ ተማሪ ሙሳ ከድር (የብርቱ ተወዳዳሪ የክብር ሽልማት) እና ሌሎችም የዚሁ እያየንለት ያለው ውጤቶች ናቸው።

የሰው ልጅ ከሚኖርባት ምድር ባሻገር በዩኒቨርሲቲ ወይም በሕዋ ውስጥ ስላሉ ነገሮች በየጊዜው የሚያደርጋቸው ምርምሮችና ጥናቶች፣ የሚደርስባቸው ውጤቶች የአዕምሮውን ምጥቀት የሚያሳዩ አስገራሚ ክስተቶች ናቸውና ወጣት ተማሪዎች ስፔስ ሳይንቲስት ለመሆን ቢጓጉ ከቶም ስህተት ሊሆን አይችልም። ወይም፣ ወደ ሌላ የጥናት መስክ ይሄዱ ዘንድ ጫና ሊደረግባቸው አይገባም። ይህንን ስንል ከአዲስ ዘመን ጋር ቆይታ ያደረገውና በውድድሩ ለሀገሩ የብር ሜዳሊያ ያስገኘው ተማሪ ፍትሕ ግርማ እና ጓደኞቹ ያለ ምንም መሰናክል ያሰቡበት ይደርሱ ዘንድ ከወዲሁ በመመኘት ነው።

የስፔስ ሳይንስ ጥናት ለዓለም ሥልጣኔና እድገት፣ ለአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች መፈጠርና ለሰው ልጆች አኗኗር ምቹ ሁኔታዎችን ከመፍጠር አንጻር እያበረከተ ያለው አስተዋጽኦ ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለም፤ በመሆኑም እነዚህን የስፔስ ሳይንስ አበርክቶዎች ለይቶ ለማወቅ ካለ ጥልቅ ፍላጎት፣ ልክ እንደነ ፍትህ ግርማ ሁሉ፣ ወጣቶች ዝንባሌያቸው ወደዚህ የጥናትና ምርምር መስክ ቢሆን ትክክል ናቸውና ወደ ሌላ ሊጠመዘዙ አይገባም።

በጽንሰ ሃሳብ ደረጃ ስፔስ ሳይንስ ለሀገራችን አዲስ ጉዳይ አይደለም። ማለትም፣ ከዘመናዊ የትምህርት ተቋሞቻችን መፈጠር በፊት በጥንት ሊቃውንቶቻችን ዘንድ (ለምሳሌ የአስትሮኖሚ እውቀት) "ህያው" የነበረ ሲሆን፤ ስሙን እያዘመነ ከመምጣቱ በስተቀር የሀገር በቀል እውቀት ባለቤትና ሊቃውንት የነበሩት ቀደምት ልሂቃን ዘንድ ("አቡሻክር"ን ያስቧል፤ "መጽሐፈ ሄኖክ"ን ያነባል) ጉዳዩ መሬት ይዞ ተግባራዊ ሲደረግ ኖሯል።

ስፔስ ሳይንስ እንደ አንድ ዘመናዊ ተቋም በሀገራችን ከተቋቋመና ወደ ሥራ ከገባ እድሜው ሩቅ አይደለም። ይሁን እንጂ ወደ ሰፋፊ ሥራዎችና ዜጎች ልብ ውስጥ በመግባት ቀልብ መሳብ ሲጀምር ጊዜ አልፈጀበትም። ተቋሙም አዳዲስ አሰራሮችን፤ ተሞክሮዎችንና ውጤቶችን ይዞ ወደ ሕዝብ መውረድ በመቻሉ ቅቡልነቱ ባልተጠበቀ ፍጥነት እየጨመረ በመሄድ ላይ ነው።

መግቢያችን ወደ እራሳችን፣ ወደ ስፔስ ሳይንስን የሚመለከተው ተቋም (በፊት የነበረውን "ስፔስ ሳይንስ" ስያሜ ከ"ካርታ ሥራዎች ባለሥልጣን" ጋር ከተዋሀደ ጀምሮ "የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት" አድርጓል) ለመሄድ እንደ መንደርደሪያ የተጠቀምንበት መሆኑን እየገለፅን ተቋሙ ከሚያከናውናቸው በርካታ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ተግባራት መካከል አንዱ ወደ ሆነው፣ ለወጣት ተማሪዎች ስለሚሰጠው ልዩ የክረምት ትምህርትና ስልጠና እንሂድ።




ተማሪ ፍትህ ግርማ

እንደ ሌሎች፣ በተለይም በዘርፉ አስቀድመው እንደ በለፀጉትና በዘርፉ ዝንባሌና ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው አዳዲስ ትውልዶችን ለማብቃትም አበክረው እየሠሩ እንዳሉት ሀገራት ሁሉ ኢትዮጵያም በዚህ ዘርፍ እየሰራች ነውና ብትዘገይም እየፈጠነች ለመሆኗ ጥሩ ማሳያ ሲሆን፤ በተለያዩ የጥናት መስኩ ዘርፎች (በስፔስ፣ በአስትሮኖሚ፣ በፊዚክስ፣ በጂኦዴሲና ተዛማጅ መስኮች) ልዩ ተሰጥኦ ያላቸውን ሕፃናት ለማብቃት የሚደረጉ ዓለም አቀፍ ውድድሮች (ለምሳሌ፣ ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የተወዳደረችበት ዓለም አቀፍ አስትሮኖሚ ኦሎምፒያድ (OWAO2024)) ላይ በመሳተፍ ከልምድና እውቀት በዘላለም አሸናፊነትን እየተላመደች በመምጣት ላይ መሆኗ የሚያበረታታ ነው። ከእንግዳችን ፍትህ ግርማ ማብራሪያም የተረዳነው ይህንን ነው።

"በቅርቡም 'Open World Astronomy Olympiad' በሚል ፕሮግራም ላይ ውድድር አድርገው ሜዳሊያ ይዘው እስከ መምጣት የደረሱ" ሰልጣኞች መኖራቸውን (አንድ የብር ሜዳሊያ፣ ሶስት የነሃስ ሜዳሊያ እና የእውቅና ሰርተፊኬት ይዘው የተመለሱ ሲሆን፤ በአጭር ጊዜ ዝግጅት ይህንን ውጤት ማምጣታቸው አስመስግኗቸዋል)። ወደ እለቱ ዝግጅታችን ስናመራ ጉዳያችን "ኢትዮ ስፔስ ኪድስ ክለብ" ሆኖ እናገኘዋለን።

በስፔስ ሳይንስ እና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት ተመራማሪ እና ቡድኑን ወደ ሩሲያ (እ.አ.አ. ከሴፕቴምበር 15 እስከ 22 ቀን 2024፣ በሩሲያ የትምህርት ማዕከል በሆነችው፣ ተማሪዎች ሳይንሳዊ ምርምሮችን የሚያደርጉባትና ለጉብኝት ክፍት የሆኑ ታላላቅ የምርምር ማዕከሎችም የሚገኙባት ሶቺ ክፍለ ግዛት - ሳይረስ ከተማ) ለውድድር ይዘው የተጓዙት ኢንጂነር ግዮን አሸናፊ (አዲስ ዘመን፣ ጥቅምት 2 ቀን 2017 ዓ.ም) "ከነበረው አጭር የዝግጅት ጊዜ፣ ከፈተናው ክብደት እና ከተወዳዳሪዎቹ ጥንካሬ አንጻር ታዳጊዎቻችን ያሳዩት የውድድር ብቃት የሚደነቅ" እና ብሩህ ተስፋን አመላካች ነው።

በጉዳዩ ላይ ያነጋገርነውና የብር ሜዳሊያን ያገኘው፤ ወደፊት ኮምፒውቴሽናል አስትሮፊዚክስ በማጥናት ሀገሩን የበለጠ ማገልገልና ማስተዋወቅ የሚፈልገው ፍትህ ግርማም የሚለው ይሄንኑ ነው። እንደ ፍትህ አስተያየት የሌሎች ሀገራት ተወዳዳሪዎች ለአንድ ዓመት ያህል ዝግጅት አድርገው ለውድድሩ የቀረቡ ሲሆን፣ የኢትዮጵያ ቡድን ግን በጣም አጭር ለሆነ ጊዜ በመዘጋጀት ነው ወደ ውድድሩ የገባው። ይህ ወደ ፊት እንደሚሻሻል ተስፋ አለ።

ይህ ክለብ፣ በኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት አማካኝነት በስፔስ ሳይንስና ጂኦስፓሻል ዘርፍ ልዩ ተሰጥኦና ዝንባሌ ያላቸውን ታዳጊ ሕፃናት የበለጠ ለማብቃት በሚል የተቋቋመ የሥልጠና ማዕከል በተለያዩ ፕሮግራሞቹ አማካኝነት ፍላጎትና ብቃት ያላቸውን ታዳጊዎች እያበቃ እንደሚገኝ በስፔስ ሳይንስ እና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት የኢትዮ ስፔስ ኪድስ ክለብ አስተባባሪ አቶ አልዓዛር ስዩም ይናገራሉ። በእስከዛሬዎቹ የአራት ዙር ስልጠናዎችም 411 (325ቱ ከክልሎች የመጡ) ተማሪዎችን ማስመረቁንም ይጠቅሳሉ።

ክለቡ ከተቋቋመ አራት ዓመታትን አስቆጥሯል። የመጀመሪያውን ሥልጠና መስጠት የጀመረው በዘርፉ ልዩ ተሰጥኦና ዝንባሌ ያላቸውን ሰባት ታዳጊዎች በመያዝ እንደሆነ የሚያስረዱት የክበቡ አስተባባሪ ክበቡ፤ በስፔስ ሳይንስ ዘርፍ ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው ታዳጊዎች በመገናኛ ብዙኃን እየተጋበዙ ስለስፔስ ሳይንስ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ተሰጥቷል። ተቋሙ እነዚህን ታዳጊዎች በአንድ የሥልጠና ማዕከል አድርጎ እገዛ ቢያደርግላቸው ነገ በዘርፉ የሀገራችንን ስም የሚያስጠሩ ተመራማሪዎችን ማፍራት ይቻላል በሚል እምነት ተቋቁሟል። ለአራት ዓመት የሚሆን የትምህርት ፕሮግራም ቀርጾ ወደ ሥራ መግባቱን ነው የሚናገሩት።

የስልጠናው ቅደም ተከተላዊ ሂደቱም በመጀመሪያው ክረምት በጂ.አይ.ኤስ፣ በሳተላይት ሳይንስ፣ በሮኬት፣ በአስትሮኖሚ እና በአስትሮ ፊዚክስ፣ በፕላኒታሪ ሳይንስ እና በጂኦዴሲ ጽንሰ ሃሳቦች (ቲዮሪዎች) ላይ በክረምት መርሃ-ግብር መሠረታዊ እውቀት እንዲጨብጡ ይደረጋል። በሁለተኛው የክረምት መርሃ-ግብር ደግሞ እነዚህን ከተግባር ጋር አያይዘው ይማራሉ። በሶስተኛው የክረምት መርሃ-ግብር ትምህርታቸውን በግሩፕ ሆነው ፕሮግራሞችን ቀርጸው እንዲሠሩ እና በአራተኛው ዓመት በግል ወይም በተናጠል ጥሩ ፕሮጀክት ይዘው እንዲሠሩ ይደረጋል። በአጭሩ፣ አቶ አልዓዛር እንደነገሩን ከሆነ በኮርሱ ከቲዮሪ ጀምሮ የተግባር ሥልጠና ሳይቀር ይሰጣል።

ከተግባራቶቹ መካከል በተቋሙ ኢንኩቤሽን ሴንተር አማካኝነት ስታርትአፖችን መደገፍ፤ እንዲሁም ባለ ተሰጥኦ ተማሪዎችን መደገፍ እና ማብቃት የሆነው የስፔስ ሳይንስ እና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት በሰባት ተማሪዎች የጀመረውን ስልጠና በማሳደግ 50 ተማሪዎችን ተቀብሎ ከቲዮሪ ጀምሮ (በቡራዩ ማሰልጠኛ ማዕከል) የተግባር ሥልጠና በመስጠት ላይ እንደሚገኝ አስተባባሪውን ጠይቀን ተረድተናል።

በሁለተኛው ዙር የገቡ ሠልጣኞች በዚህ ዓመት 16 ፕሮጀክቶችን ቀርጸው የተለያዩ ተግባራትን በመሥራት ወደ ሶስተኛው ዙር ያለፉ መሆናቸውን፤ እንዲሁም አራተኛ ዓመት የክረምት መርሃ-ግብር ትምህርት ላይ ያሉት የመጀመሪያዎቹ ሰባት ተማሪዎች በአሁኑ ሰዓት ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚገቡበት የትምህርት ደረጃ ላይ የሚገኙ መሆናቸውን ለማወቅ ችለናል።

የተለያዩ ዓለም አቀፍ ግንኙነቶችን በመፍጠር ልጆቹ ከመክሊታቸው ጋር እንዲያገናኙ ሥልጠና ማዕከሉ ጉልህ እገዛ እያደረገ መሆኑን የሚናገሩት አቶ አልአዛር በአሁኑ ሰዓት አንድ ተማሪ ዓለም አቀፍ ግንኙነት በመፍጠር ወደ ካሊፎርኒያ ዩኒቨርሲቲ ሄዶ የነፃ ትምህርት በመማር ላይ እንደሚገኝ፤ ሌሎችም ተመሳሳይ እድል የማግኘት እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ መሆናቸውንም ያስረዳሉ።

በስፔስ ሳይንስ እና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት የኢትዮ ስፔስ ኪድስ ክለብ አስተባባሪ አቶ አልዓዛር ስዩም እንደሚሉት፤ ወደ ተቋሙ እንዲሁ ዘው ተብሎ አይገባም። በማዕከሉ ሥልጠና የሚሰጣቸው ተማሪዎች በስፔስ ሳይንስ ዘርፍ ዝንባሌና ተሰጥኦ ያላቸው ሆነው የሚሰጠውን የመግቢያ ፈተና ማለፍ የሚችሉ ናቸው። በተጨማሪም በዚህ ዘርፍ የተለየ ተሰጥኦ ያላቸው ስለመሆኑ የሚያሳይ ሥራ ካላቸውም ያንን ይዘው በመቅረብ ስለጉዳዩ ያብራራሉ። ልጆቹ ተቀባይነት ካገኙ መደበኛ ትምህርታቸውን በማይነካ መልኩ፣ በክረምት መርሃ-ግብር ለአንድ ወር ከአስራ አምስት ቀን ሥልጠናው ይሰጣቸዋል።

ሰልጣኝ ተማሪዎቹ የራሳቸውን ዲዛይን ቀርጸው ከ95ሺህ የጫማ ከፍታ በላይ ባሎን ልከው ሙከራዎችን እስከ ማድረግ መድረሳቸውን የሚናገሩት አቶ አልዓዛር አንዳንድ ጊዜ በበጋ ወቅት ውጭ ሀገር ካሉ ድርጅቶች ጋር በመነጋገር በቨርቿል ተጨማሪ ሥልጠና የሚሰጥበት ሁኔታም አለ። ለምሳሌ አምና ሰኔ ወር አካባቢ የተመረቁ ልጆች ፋሴሳ የሚባል ድርጅት ከቦይንግ ጋር በመተባባር ባዘጋጀው የቨርቿል ሥልጠና ኤሮ ስፔስን በተመለከተ ለአምስት ወር የቆየ ሥልጠና ወስደዋል።

"እንደ ተቋም የተያዘው ግብ ከማሰልጠኛ ማዕከሉ የተመረቁ ልጆች ከስታርትአፕ ኩባንያ ጋር በመሆን የራሳቸውን ኩባንያ አቋቁመው በስፔስ ዘርፍ እንዲሰሩ ማስቻል ነው። በአሁኑ ሰዓት እንደ ሀገር ሁለት ኩባንያዎች ተቋቁመዋል። አንዱ ኩባንያ ስፔስ ኪድ ክለብ የነበሩ አራት ልጆች ያቋቋሙት ነው። በዚህ ኩባንያ ውስጥ ለተለያየ ዓላማ የሚውል ድሮን ያለማሉ። ያንን ድሮን በፋብሪካ በብዛት አምርተው ወደ ገበያ ማውጣት የሚል እቅድ ይዘው እየሠሩ ነው"። እንደ አቶ አልዓዛር ገለጻ፤ እንደ ሀገር እንደዚህ ዓይነት ክለብ መቋቋሙ ከፍተኛ ጥቅም አለው። በተለይም በዘርፉ ዝንባሌ ያላቸውና በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ችሎታና ፍላጎት እያላቸው ተደብቀው የቀሩ ልጆችን ወደ ሜዳው ለማምጣት ጥሩ እድል ይፈጥራል። በያዝነው ዓመት ወደ ዩኒቨርሲቲ እየገባ ያለው የዛሬው እንግዳችንም የረጅም ጊዜ እቅዱ ይሄው ነው። የራሱ የሆነ ኩባንያ አቋቁሞ የሰውን ልጅ መርዳትና ሀገሩንም ማስጠራት። በስፔስ ሳይንስ እና ጂኦስፓሻል

ኢንስቲትዩት ተመራማሪ እና ቡድኑን ወደ ሩሲያ ለውድድር ይዘው የተጓዙት ኢንጂነር ግዮን አሸናፊ እንደ ተናገሩት፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከተደረገው ውድድርና ውጤት አስፈላጊውን ልምድ በመውሰድ "የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስ ኪድስ ክለብ አዋርድ" ተቋቁሟል። በመሆኑም ሁሉም፣ አቅም፣ ፍላጎትና መሻት ያላቸው ወጣት ተማሪዎች ሁሉ ወደዚሁ ክለብ እንዲመጡ ተጋብዘዋል። ሀገር አቀፍ ውድድሮች ላይ በመሳተፍም ለዓለም አቀፍ ውድድሮች ራሳቸውን ከወዲሁ እንዲያበቁ ተጠይቀዋል።

በመጨረሻም፣ የመጪውን ዘመን የስፔስ ሳይንስ ባለሚሎች ከወዲሁ ማፍራት እንዲቻል፣ መምህራንና "ወላጆች በስፔስ ሳይንስ እና በፈጠራ ዘርፍ የተለየ ተሰጥኦና ዝንባሌ ያላቸውን ልጆች ከህልማቸው ጋር እንዲገናኙ ከተቋሙ ጋር የማስተዋወቅና የተሻለ እውቀት እንዲያገኙ የማድረግ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ" አቶ አልዓዛር ጥሪ ያቀርባሉ።

# በሕገ ወጥ ስደት እየተፈተነች ያለችው ድሬዳዋ

**አመለወርቅ ከበደ**

ድሬዳዋ ከተማ በምሥራቁ የኢትዮጵያ ክፍል የምትገኝ ከተማ ናት። ከተማዋ የኦሮሚያን ክልል እና የሶማሌን ክልል የምታዋስን ሲሆን፤ በሀገሪቱ ካሉት ሁለት የከተማ አስተዳደሮች አንዷ ናት። ድሬዳዋ ከተማ በኢትዮጵያ ካሉ ከተሞች አራተኛዋ ዝነኛ ከተማ ናት።

ከተማዋ ሰፊ የንግድ እንቅስቃሴ ያለባት እና የተለያየ የአኗኗር ባሕል ያለባት ከተማ ናት። የፍቅር ከተማ፣ የበረሀዋ ገነት የሚባሉ ቅጽል መጠሪያ አላት። ድሬዳዋ በምሥራቁ አቅጣጫ ለኢትዮጵያ ድንበር አካባቢ ያለች እንደመሆኗ እና በመተማ በኩል ያለው መንገድ በመዘጋቱ ሥራ ፍለጋ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ የሚሻገሩ ከተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍል የሚመጡ ሕገ ወጥ ፍልሰተኞች አሁን ላይ ወደ ከተማዋ ፍልሰታቸው እየጨመረ መጥቷል።

ፍልሰተኞቹ ድንበር ለመሻገርም ሆነ ተመልሰው ወደ አካባቢያቸው ሲመለሱ፤ ባጋጣሚ ያሰቡት ሳይሳካላቸው ሲቀር እዛው ከተማው ላይ የሚቀሩበት ሁኔታ አለ።

በሌላ በኩል እንደ ሀገርም ሆነ እንደ ዓለም አቀፍ ስለ ሕገ ወጥ ስደት አስከፊነት በርካታ ነገር ተብሏል። ለስደት የወጡ ዜጎች የሚያጋጥማቸው አደጋ በተለያዩ ዘጋቢ ፊልሞች፣ ዜናዎች እና ሌሎች የጥበብ መንገዶች ሲነገር ቆይቷል፤ አሁንም እየተነገረ ነው።

ዜጎችን ለሕገ ወጥ ስደት በሚዳርጉ ደላሎች ላይ በተለያዩ ጊዜያት ርምጃ መወሰዱም ይነገራል። ነገር ግን አሁንም ቢሆን እነዚህ ሕገ ወጥ ደላሎች አሰራራቸውን በመቀየር ሥራቸውን ማስኬዳቸው አልቀረም።

ዛሬ በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ የማህበራዊ ዘርፍ ኃላፊ አቶ አብዱረህማን ሙሳ አደን ጋር፤ በከተማው እየጨመረ የመጣውን የሕገ ወጥ ፍልሰተኞች ቁጥር፣ ለመፍለሳቸው መንስኤ፣ ችግሩን ለመቅረፍ እየተሰራ ስላለው ጉዳይ እና መሰል የሆኑ ጥያቄዎችን አንስተናል። በከተማ አስተዳደሩ የሴቶች ጥቃት ለመከላከል ምን ተሰራ? ምን ውጤት ተገኘ? የሚሉትን ጥያቄዎች አካትተን ከኃላፊው ጋር ቆይታ አድርገናል። መልካም ንባብ!

**አዲስ ዘመን፡- የድሬዳዋ ከተማ ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊነቶች ምንድን ናቸው?**

**አቶ አብዱረህማን፡-** አጠቃላይ እንደ ሀገርም ሆነ እንደ ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የሴቶች፣ ሕፃናት እና ማህበራዊ ዘርፍ የሚሰራው ትላልቅ ሥራዎችን ነው። በስፋት የሚሰሩ ሥራዎች ሰው ተኮር ሥራዎች ናቸው።

ሴቶች ላይ፣ አካል ጉዳተኝነት ላይ፣ ድህነት ቅነሳ ላይ፣ አረጋውያን ላይ፣ ሕገ ወጥ ስደትን መከላከል ላይ ያተኮሩ ሥራዎች ይሰራሉ። በሂደት ትውልድን የማነጽ ሥራ ስለሆነ በዘርፉ የሚሰሩት በርካታ ተግባራት ናቸው።

እውቀት እና አቅም ያላቸው አረጋውያንም እውቀትና ክህሎታቸውን እንዲያካፍሉ እየተደረገ ነው። በኢኮኖሚው ተጠቃሚ የሚሆኑበት መንገድ እየተመቻቸ ነው። እንደ ሀገር ካለው የሕዝብ ቁጥር 20 በመቶ የሚሆኑት አካል ጉዳተኞች መሆናቸው ይነሳል፤ እንደ ድሬዳዋ ከተማም አካል ጉዳተኞችን በአካቶ ትግበራ ተጠቃሚ ለማድረግ ሰፊ ሥራ እየተሰራ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በከተማ አስተዳደሩ ከሴቶች ጋር ተያይዞ የሚነሱ ችግሮች ምንድን ናቸው? እንደ ቢሮ በሴቶች ረገድ ምን ዓይነት ሥራዎች እየተሰሩ ነው?**

**አቶ አብዱረህማን፡-** ከለውጡ በፊት እና ከለውጡ በኋላ ባሉ ነገሮች በጣም ሰፊ ልዩነት ነው ያለው። አሁን ላይ ለሴቶች፣ ለሕፃናት፣ ለአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ትልቅ ትኩረት ተሰጥቷል እንደ ሀገርም እንደ ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርም እየተሰራ ነው።

እንደ አጠቃላይ የልማት ተጠቃሚ እንዲሆኑ እና የልማቱ ተሳታፊ እንዲሆኑ የተጀመሩ ሥራዎች አሉ። በአሁኑ ወቅት ሴቶችን በኢኮኖሚ እና በአቅም የመደገፍ ሥራዎች ተጀምረዋል። በዚህም ሴቶችን የማደራጀት፣ ሴቶች በኢኮኖሚ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማድረግ እና አካቶ ትግበራ ላይ የሴቶች ተሳትፎ በጣም የመጨመር ሁኔታ አሳይቷል።

የሴቶችን ጥቃት ለመከላከል ኢትዮጵያ ተቀናጅታ በሰራቻቸው ሥራ፤ ዓለም አቀፍ እውቅና ማግኘቷ ይታወሳል፤ ይህን ተከትሎ ክልሎች በሴት ልጅ ጥቃትን ለመከላከል በሰሩት ሥራ እውቅና ሲሰጣቸው፤ እውቅና ካገኙ ክልሎች አንዱ የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ነው።

ከዚህ ጋር ተያይዞ የሴቶች ጥቃት በድሬዳዋ አስተዳደር የቀነሰበት ሁኔታ አለ። የተሻለ አፈጻጸም ካላቸው ቢሮዎች አንዱ የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የሴቶች ጥቃትን ከመከላከል ረገድ ቢሮው እውቅና ማግኘቱን የገለጹበት ሁኔታ አለና፤ ከዚህ በፊት የጉዳዩ አስከፊነት ምን ያህል ነበር? የተሰሩ ሥራዎችና አሁን ያለው ሁኔታስ ምን ይመስላል?**

**አቶ አብዱረህማን፡-** ቀደም ብዬ እንዳነሳሁት ከዚህ በፊት ለሴቶችና እንደ አጠቃላይ ለዘርፉ የሚሰጠው ትኩረት በጣም ያነሰ ነበር፤ ሁለተኛው ነገር አሁን ላይ ለዘርፉ ትኩረት ለመስጠት በማሰብ፤ ያቀድነው እቅድ በጣም የተለጠጠ እቅድ ነው። ያቀድነውም 50 በመቶ እና ከዛ በላይ እናሳካለን ብለን ነው።

ሴቶች እንደመሆናቸው የኢኮኖሚ አቅማቸውን የማጠናከር ሥራ ተሰርቷል። በዛው ደረጃ የሴቶችን መብት በማረጋገጥ ደረጃ ከፍትህ አካላት ጋራ እየተሰራ ነው። ለዚህም ሴቶች ጥቃት ካጋጠማቸው ደውለው እንዲያሳውቁ ነፃ የስልክ መስመር ተዘጋጅቷል። የስልክ መስመሩ ያለው በድሬዳዋ ፖሊስ ኮሚሽን ነው። ችግር ሲያጋጥም ማንኛውም ሰው በዛ እንዲደውሉ የተመቻቸ ነው። በዚህም ጥቆማዎች ሲደርሱ ወዲያውኑ ምላሽ የመስጠት ነገር አለ።

ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርን እንደ ሀገር አቀፍ አንድ ለየት የሚያደርገው፤ የጥቃት ማገገሚያ ማዕከል የሚል ትልቅ ህንጻ ተገንብቷል። ይህም ጥቃት የሚደርስባቸው ሴቶች የሚያገግሙበት ማዕከል ነው። ከጤና ቢሮ ጋር በመነጋገር አንድ ሆስፒታል ላይም የጥቃት ማዕከል ተገንብቶ ከጥቃት የማገገሚያ እና የኢኮኖሚ ማጠናከሪያ ሥራ እየሰራ ነው የሚገኘው።

ጥቃትን ከመከላከል ረገድ በሚዲያዎች ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራዎች በስፋት ተሰርቷል። ሌላው ነገር እንደሚታወቀው ድሬዳዋ አካባቢ ያለው ማህበረሰብ ቅን ነው። ስለዚህ ሴቶችን ከማህበረሰብ ለይቶ የማግለል ነገር የለም። ከመጀመሪያውም እንደ ባሕሉ ለሴቶች በጣም ትኩረት ይሰጣል።

ከተማውም ሰላማዊና ሰው ተዋዶ የሚኖርበት እንደመሆኑ ብዙም በሴቶች ላይ የሚደርስ ማህበራዊ ተጽዕኖ የለም። በተጨማሪም ስልጡን ሕዝብ በመሆኑ ከዚህ በፊትም ቢሆን ሴቶች ላይ የሚደርሰው ተጽዕኖ ብዙም አልነበረም። ነገር ግን ባለፉት አምስት ዓመታት ከሴቶች ጋር ተያይዞ ሰፋፊ ሥራዎች ተሰርተዋል።

**አዲስ ዘመን፡- ሴቶች ላይ የሚደርሱ የተለያዩ ጥቃቶች አሉ፤ ችግሩን ለመቅረፍ ባለፉት አምስት ዓመታት የትኞቹ ላይ ነው ትኩረት ተደርጎ የተሰራው?**

**አቶ አብዱረህማን፡-** ባለፉት አምስት ዓመታት ትኩረት ተሰጥቶ የተሰራው ቤተሰብ ማጠናከር ላይ ነው። ሌላው ደግሞ በሁለት አካላት በፍትህ እና በሚዲያ አካላት ላይ የተሰራ ሥራ ነው።

ቤተሰብን ማጠናከር ሲባል አባት ሊሆን ይችላል፤ ወንድም ሊሆን ይችላል፤ እናት ልትሆን ትችላለች ችግር በሚፈጠርበት ወቅት ቶሎ ብለው ወደ ሕግ አካላት ከመሄድ ይልቅ፤ እያንዳንዱ የራሱን ኃላፊነት በመውሰድ ችግሩን እዛው ተነጋግሮ በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ የማድረግ ሥራ ነው።

ምክንያቱም እያንዳንዱ ቤተሰብ ውስጥ ነው ሴቷ የምትጠቃለለው፤ ቤተሰብን የማጠናከር ሥራ በዋነኝነት የተያዘው ለዛ ነው። እንደ ሀገር ደረጃም የተያዘው የቤተሰብ ጉዳይ ነው። ስለዚህ እንደ ከተማ አስተዳደር ቤተሰብ ላይ ሰፋፊ ሥራ በመሰራቱ ጥቃቱ ሊቀንስ ችሏል። ቤተሰብ ማለት ሀገር ነው፤ ስለዚህ ሁሉም አካባቢዎች በዚህ ላይ ቢሰሩ መልካም ነው የሚል እምነት አለኝ።



አቶ አብዱረህማን ሙሳ አደን

> **ቤተሰብን ማጠናከር ሲባል አባት ሊሆን ይችላል፤ ወንድም ሊሆን ይችላል፤ እናት ልትሆን ትችላለች ችግር በሚፈጠርበት ወቅት ቶሎ ብለው ወደ ሕግ አካላት ከመሄድ ይልቅ፤ እያንዳንዱ የራሱን ኃላፊነት በመውሰድ ችግሩን እዛው ተነጋግሮ በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ የማድረግ ሥራ ነው**

ሌላኛው ነገር የሴቶችን ጥቃት ከመቀነስ ረገድ ከእኛ ጋር ትላልቅ ሥራዎችን ሲሰሩ የነበሩ እና ሊመሰገኑ የሚገባቸው መንግሥታዊ ያልሆኑ ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች አሉ። በእነሱ ርዳታም ጭምር ጥቃቶች ሊቀንሱ ችለዋል ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የሴቶች ጥቃት በምን ያህል መጠን መቀነስ እንደተቻለ በቁጥር ቢገልጹ?**

**አቶ አብዱረህማን፡-** ከሴቶች ጥቃት ጋር ተያይዞ ሰፋፊ ሥራዎች ተሰርተዋል፤ በዚህም የጥቃት መጠኑ ከ60 እስከ 63 በመቶ ቀንሷል። ቅድም እንዳነሳሁት ድሬዳዋ ላይ የሴቶች ጥቃት ብዙም የተለመዱ አይደሉም። በአካባቢው እንደዚህ ዓይነት ሥነ ምግባርም የለም። እንደቢሮም የበለጠ በሴቶች ረገድ ከአጋር አካላት ጋር በመሆን የተሰራው ሥራ ሴቶችን በኢኮኖሚ የማጠናከር እና የግንዛቤ ሥራ ነው።

በዚህም ሴቶችን በአስተሳሰብ የማጠናከር ሥራ የተሰራ ነው እንጂ፤ የሴቶች ጥቃት ብዙም በዛ ደረጃ በተለየ ሁኔታ የከፋ አይደለም። ግን ባለን እቅድ አኳያ ተሻሽሎ ብዙ ሥራ ተሰርቷል የሚል አንድምታ ነው ያለን።

**አዲስ ዘመን፡- ከሴት ልጅ ግርዛት ጋር ተያይዞ ያለው ነገር ምን ይመስላል?**

አቶ አብዱረህማን፡- የሴት ግርዛት ከሃይማኖትም ጋር ተያይዞ የቆየ ባሕል ነው። ሰው ሃይማኖት የሚፈቅድ ይመስለዋል እንጂ አይደለም። በዚህ ረገድ ያደረግነው ነገር ከሁሉም አካላት ጋር ጥምረት መፍጠር ነው። ከሃይማኖት አባቶች፣ ከፍትህ አካላት እንዲሁም ከማህበረሰብ ውስጥ ተሰሚነት ካላቸው ሰዎች እና ግርዛት የሚያከናውኑ ሰዎችንም የጥምረቱ አካል በማድረግ በየትምህርት ቤቱ ባሉ ሚኒሚዲያዎች የግንዛቤ ሥራ ተሰርቷል።

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

## በሕገ ወጥ ስደት እየተፈተነች ...



ከገጽ 9 የዞረ

አሁን ላይ የሴት ልጅ ግርዛት በብዙ ቁጥር ቀንሷል። ምናልባት በቀጣይ ትውልድ ይህ ነገር ይኖራል የሚል ሃሳብ የለኝም። ምክንያቱም ቤተሰብ እንደ ጃንጥላ ነው። በዚህ መሰረት ቤተሰብን የማጠናከር እና ከሴት ልጅ ግርዛት ጋር ተያይዞ ግንዛቤ እየተሰራ ነው።

የሃይማኖት ተቋማትም በየመስጊዱ፣ በየቤተክር ስቲያኑ እና በየጸሎት ቤቱ የሴት ልጅ ግርዛት ያለውን ጉዳት እንዲረዱት የማስተማር እና ለተከታዮቻቸው ግንዛቤ እንዲሰጡ ሥራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል። በቀጣይም ይህ ተግባር ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፦ ከግንዛቤ ሥራው ጎን ለጎን አንዳንዴ በድብቅ የሴት ልጅ ግርዛት የሚከናወንበት ሁኔታ አለ፤ በዚህ ረገድ የሕግ ቁጥጥሩ ምን ይመስላል?**

**አቶ አብዱረህማን፦** ከሴት ልጅ ግርዛት ጋር ተያይዞ ያለው አስከፊነት በቅድሚያ ግንዛቤ ለሴት ልጆች ይሰጣል። እንደዚህ ዓይነት ጥሰቶች በሚፈጠሩበት ወቅት ትምህርት ቤት ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን በነፃ የስልክ መስመር እንዲያሳውቁ ይደረጋል።

እንደዚህ ዓይነት ጥሰቶች ሲከሰቱ ከማህበረሰቡ ከተወጣጣው የጥምረት አካላት ጋር በመቀናጀት ይሰራል። በተጨማሪም ቢሮው ከፍትህ አካላት ጋርም ይሰራል እንደዚህ ዓይነት የሕግ ጥሰቶች ሲኖሩ፤ ወንጀለኞቹ ላይ ርምጃ ይወሰዳል።

ስለዚህ ይህን ጥቃት ለመከላከል ቀድሞ የሚሰጠው ግንዛቤ ነው። ነገር ግን በረጅም ጊዜያት እንደዚህ ዓይነት ተፈጥሮ ጥቆማ ሲደርስ ተጠያቂ እንዲሆኑ ይደረጋል።

**አዲስ ዘመን፦ በከተማ አስተዳደሩ የሴቶች ጥቃት ዝቅተኛ እንደሆነ ገልጸው ነበረ፤ በዚህ ረገድ ለሌሎች ክልሎች እንደተሞክሮ ሲነሳ የሚችል ነገር ምንድን ነው?**

**አቶ አብዱረህማን፦** በአካባቢው ለሴት ልጅ ትልቅ ቦታ ከመስጠት ረገድ ያለው ሥነ ምግባር ትልቅ የሚባል ነው። ለዚህም ደግሞ አንዱ ምክንያት፤ ማህበረሰቡ የነቃና ስልጡን መሆኑ ነው። ይህን ስል ግን ሌላው የማህበረሰብ ክፍል ስልጡን አይደለም ማለቴ እንዳልሆን እንዲታሰብልኝ እፈልጋለሁ። ስለዚህ የሴት ልጆችን ጥቃት ለመከላከል ማህበረሰብን ማንቃት ያስፈልጋል እላለሁ።

በከተማ አስተዳደሩ እንደዚህ ዓይነት ሥነ ምግባር እንዲፈጠር ያደረገው ማህበረሰቡ አንዱ ከአንዱ ጋር ያለው ውህደት ነው። የአካባቢው ሕዝብ አንዱ ከአንዱ ጋር ያለው መተሳሰብ፤ አብሮ መብላት ብቻ ሳይሆን፤ በሃሳብ የመደጋገፍ ነገርም አለ። ስለዚህ ማህበረሰቡ ግላዊነት ሳይሆን፤ አብሮነትን የሚያንጸባርቅ ነው። ሌላው ማህበረሰብ ይህንን ልምድ ቢቀስም የሚል ሃሳብ አለኝ።

በሌላ በኩል ማንሳት የምፈልገው ነገር ከሕገ ወጥ ስደት ጋር ተያይዞ ያለውን ነገር ነው። ድሬዳዋ ለምሥራቁ የሀገራችን ክፍልና እና እንደ አጠቃላይ ለኢትዮጵያ ስትራቴጂክ ቦታ ላይ የምትገኝ ከተማ ነች። ለወደብም በጣም ቅርብ ቦታ ላይ ናት። ከጅቡቲ 300 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ያለች ናት።

ከተለያዩ ቦታዎች ከደቡብ፣ ከአማራ፣ ከኦሮሚያ እና ከትግራይ ክልል ወደ መካከለኛው ምስራቅ ሥራ ፍለጋ የሚመጡ ሰዎች ፍሰት አሁን ላይ በከተማዋ በጣም የጨመረበት ሁኔታ እንዲፈጠር አድርጓል። በሕገ ወጥ መንገድ፣ በሕገ ወጥ ደላሎች አማካኝነት መጥተው ሳይሳካላቸው ሲቀር በከተማው ለጎዳና ሕይወት ተጋልጠው የመቅረት ነገር በስፋት ይታያል።

በተለይ የሱዳን ጦርነት ተቀስቅሶ የመተማ መንገድ ከተዘጋ በኋላ፤ የሕገ ወጥ ስደተኞች ጫና በድሬዳዋ ከተማ እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው። ወደ ስደት ሲሄዱም ሆነ ሲመለሱ ሳይሳካላቸው ሲቀር ድሬዳዋ ከተማ ውስጥ ነው የሚቀሩት።

እነዚህ ሰዎች ኢትዮጵያዊ እንደመሆናቸው በተለያየ ጊዜ ወደ ቤተሰቦቻቸው እንዲመለሱ የሚደረግ

“

**ድሬዳዋ ከተማ የሚቀሩበት ምክንያት ከቤታቸው ሲወጡ ይዘው የወጡትን ብር ሲጨርሱ እንዴት ባዶ እጅ ወደ ቤተሰብ እመለሳለሁ ብሎ የመፍራት ነገር በመፈጠሩ ነው፡፡ ይዘውት የመጡትን ብር ደላላው ይቀበልና የመሻገሩ ጉዳይ ሳይሳካ ሲቀር ወደ ጎዳና የሚወጡበት ሁኔታ ይፈጠራል**

ሥራ እንሰራለን፤ ነገር ግን ክልሎቹ በዚህ ዙሪያ በጣም ሰፊ ሥራ ሊሰሩ ይገባል። ሚዲያዎችም በግንዛቤ በኩል የራሳቸውን ድርሻ ሊወጡ ይገባል።

በሕገ ወጥ መንገድ ድንበር መሻገር በጣም አደጋ እንዳለው ሊያውቁት ይገባል። በተለይ በዚህ ጉዳይ ሴቶች በጣም ተጎጂዎች ናቸው፤ በተጨማሪም ወጣቶች እና ሕፃናትም እንደዚያ ናቸው።

**አዲስ ዘመን፦ ፍልሰተኞቹ ከአካባቢያቸውም የሚወጡበት ምክንያት ምንድነው? ከወጡ በኋላ በከተማው እንዲቀሩ የሚያደርጋቸው ምን ዓይነት ሁኔታ ነው? በጉዳዩ ዙሪያ የተሰራ ጥናት ይኖር ይሆን?**

**አቶ አብዱረህማን፦** ማግኘት ከቻልነው መረጃ አንጻር ፍልሰተኞቹ ከሚኖሩበት አካባቢ እንዲወጡ የሚያደርጋቸው ገፊ ምክንያቶች፤ ዋነኞቹ የእናትና አባት መለያየት፤ ከቤተሰብ ግጭት ጋር ተያይዞ እና ከኑሮ ሁኔታ አንጻር ነው። በዚህ ረገድ በአካባቢዎቹ ድህነት ቅነሳ ላይ መሥራት ያስፈልጋል።

ሌላው ክልሎቹ ሕገ ወጥ ፍልሰት ምን ያህል አስከፊ እንደሆነ፤ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ መሥራት ያስፈልጋቸዋል። እነዚህ ክልሎች የበለጠ መረጃ ለማግኘት እና ያለውን ችግር ለመቅረፍ ጥናት ቢያደርጉ እና ጉዳዩ ላይ ቢሰሩ የተሻለ ይሆናል የሚል እምነት አለኝ።

ድሬዳዋ ከተማ የሚቀሩበት ምክንያት ከቤታቸው ሲወጡ ይዘው የወጡትን ብር ሲጨርሱ እንዴት ባዶ እጅ ወደ ቤተሰብ እመለሳለሁ ብሎ የመፍራት ነገር በመፈጠሩ ነው። ይዘውት የመጡትን ብር ደላላው ይቀበልና የመሻገሩ ጉዳይ ሳይሳካ ሲቀር ወደ ጎዳና የሚወጡበት ሁኔታ ይፈጠራል።

ሌላው ምክንያት የድሬዳዋ ማህበረሰብ እንግዳ ተቀባይነት እና አየሩም ምቹ ነው። አየሩ ስለማይከለክለው አንድ ሰው በረንዳ ላይ ሊተኛ ይችላል። ሰው የመረዳዳት ባሕሉ በጣም ከፍ ያለ ስለሆነ ሰው እዛ ከሄደ አይመለስም። ነገር ግን አሁን ላይ ከአቅም በላይ ሆኗል፤ ፍሰቱ የድሬዳዋ ሕዝብ ፍሰት አይደለም። ወደ ጁቡቲ ለመሻገር ከሌሎች ክልሎች የሚመጡ ሕዝቦች ፍሰት ነው።

**አዲስ ዘመን፦ ፍልሰተኞቹ በስፋት የሚመጡት ከየትኛው የሀገሪቱ አካባቢ ነው?**

**አቶ አብዱረህማን፦** ኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሀረርጌ እና ምዕራብ ሀረርጌ፤ ከአርሲ አካባቢ ነው። ሌላው ከደቡብ ክልልም ይመጣሉ። ከአማራ ክልል ደግሞ ከወሎ አካባቢ እንዲሁም ከትግራይ ክልል አካባቢም የሚመጡ አሉ።

ከዚህ በፊት ትግራይ ክልል እና አማራ ክልል ያሉ ሰዎች በመተማ በኩል ነበር የሚወጡት። አሁን ግን እዛ አካባቢ ችግር ስላለ፤ ለዛ ነው ጫናው የበረታው። ስለዚህ ክልሎች በቅንጅት ሰፋፊ ሥራ እንዲሰሩ ይጠበቃል።

**አዲስ ዘመን፦ ከአካባቢው የሚወጡት በራሳቸው ተነሳሽነት ነው? ወይስ ግፊት የሚያሳድርባቸው አካል አለ?**

**አቶ አብዱረህማን፦** በብዛት ደላሎች ናቸው የሚያመጧቸው፤ እናሻግራችኋለን በሚል ብራቸውን ከተቀበሉ በኋላ የሚቀሩበት ሁኔታ ይፈጠራል። እነዚህን ሕገ ወጥ አዘዋዋሪዎች ተጠያቂ ለማድረግ የተጀመረ ሥራ አለ። በዚህ ረገድ የተቋቋመ ኮሚቴ አለ በእነዚህ በኩል የቁጥጥር ሥራውን አጠናክሮ መቀጠል ያስፈልጋል።

ሌላው ፍልሰተኞቹ ከቤታቸው የሚወጡት በአካባቢያቸው ያለ ሰው ውጭ ሀገር ሄዷል በሚል መረጃ ሳይኖራቸው የሚወጡበት ሁኔታ ነው። በስፋት ግን ሕገ ወጥ አዘዋዋሪዎች ናቸው እንዲወጡ የሚያደርጓቸው።

**አዲስ ዘመን፦ ሕገ ወጥ አዘዋዋሪዎቹ ፍልሰተኞቹ በሚኖሩበት አካባቢ ያሉ ናቸው? ወይስ ፍልሰተኞቹ ድሬዳዋ በጥቆማ ነው የሚመጡ?**

**አቶ አብዱረህማን፦** ከመካከለኛው ምሥራቅ ጀምሮ እስከ ኢትዮጵያ ድረስ፤ ሕገ ወጥ አዘዋዋሪዎቹ የራሳቸው ሰንሰለት አላቸው። በሚዲያም እንደሚታየው መንግሥት በእነዚህ ሕገ ወጥ አዘዋዋሪዎች ላይ ርምጃ ወስዷል፤ ግን አሁንም ይቀራል።

አንዱ ሲቀጣ ሌላኞቹ በየጊዜው አሰራራቸውን እየቀየሩ ስለሚሰሩ ችግሩን ለማጥፋት አዳጋች ያደርጋል። ስለዚህ አሁንም በጥናት በመለየት ርምጃ የመውሰድ ሥራ ያስፈልጋል።

**አዲስ ዘመን፦ ድንበር ለመሻገር ወደ ከተማው መጥተው የሚቀሩትን ወደመጡበት አካባቢ የመመለስ ሁኔታው ምን ይመስላል?**

**አቶ አብዱረህማን፦** በየጊዜ ወደመጡበት አካባቢ እንመልሳለን፤ ነገር ግን የቅንጅት ሥራ ይፈልጋል። ጉዳዩን ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱም አንስተናል። አሁን ላይ ትንሽ ክልሎች ካጋጠማቸው የጥሬ በጀት እጥረት ጋር እና ካሉበት ሁኔታ ጋር ተያይዞ ተግዳሮቶች አሉ። ነገር ግን ችግሩን ለመፍታት ሰፊ ሥራ ይጠይቃል።

**አዲስ ዘመን፦ በጉዳዩ ላይ እንደ ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ምን እየተሰራ ነው?**

**አቶ አብዱረህማን፦** እኛ የተለያዩ ጥናቶችን በማድረግ እንደ ከተማ አስተዳደር ሰፋፊ ሥራዎችን ጀምረናል። ስለዚህ በቀጣይ ችግሮችን ለመቅረፍ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት በጥናት የተደገፈ ሥራ እንሰራለን የሚል ሃሳብ አለኝ።

**አዲስ ዘመን፦ በጉዳዩ ላይ ለክልሎቹ፣ ለፍልሰተኞች እና ሌሎች ለሚመለከታቸው አካላት የሚያስተላልፉት መልዕክት ይኖርዎ ይሆን?**

**አቶ አብዱረህማን፦** እንደ ሀገር ጠንካራ ኮሚቴ ተዋቅሮ ሥራዎችን በቅንጅት መሥራት ያስፈልጋል። በግንዛቤው ረገድም ሀገር አቀፍ ሚዲያዎችን በመጠቀም መሥራት የግድ ይላል የሚል ሃሳብ አለኝ። በተጨማሪም በድሬዳዋ ከተማ የጨመረውን የሕገ ወጥ ፍልሰተኞች ቁጥር ለመቀነስ ክልሎች በቅንጅት ሊሰሩ ይገባል የሚልም አስተያየት አለኝ።

**አዲስ ዘመን- ለሰጡን ሰፊ ማብራሪያ እናመሰግናለን።**

**አቶ አብዱረህማን፦** እኔም አመሰግናለሁ።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## አዲስ ገበያ መፍጠር የሚፈልገው ዲዛይነር

**ሰሚራ በርሀ**

ፋሽን የሚለው ቃል በየጊዜው የሚቀያየር፣ በአንድ ወቅት ተለብሶ ተፈላጊነቱ የሚያበቃ እና ገበያ ተኮር እንደሆነ ዲዛይነር ኤርሚያስ ልዑልሰገድ ይገልጻል። ዲዛይነር ኤርሚያስ የታሪዮ ፋሽን መስራች ነው። እሱ እንደሚለው የፋሽን ሃሳብ የጊዜ ወሰን የሌለው እና የራሱን እሳቤ የያዘ ነው።

ኤርሚያስ የፋሽን ዲዛይን ሃሳብ ይዞ ብቅ ያለው ገና የ12ተኛ ክፍል ተማሪ በነበረበት ወቅት ሲሆን፤ መነሻው የራሱ ባህሪ እና ለፋሽን ያለው መረዳት ነው። የሚፈልገውን ጠንቅቆ የሚያውቅ፣ ያመነበትን ሃሳብ ለመናገር በፍጹም የማይፈራ፣ ወጣ ያለ ባህሪ እንዳለው ጠቅሶ፣ አንዳንዶች ይህን ባህሪውን እንደ ትዕቢት እንደሚቆጥሩትም ይገልጻል። እነዚህ ባህሪያት የኤርሚያስ መገለጫዎች ናቸው ይላል።

ኤርሚያስ በተማሪነቱ ወቅት ሶፍትዌር ኢንጂነሪንግ የመማር ፍላጎት ነበረው፤ ዲዛይነር የመሆን ፍላጎትን ያዳበረው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በሚያጠናቅቅበት ወቅት ነበር። ካይኒ ዌስት የተባለ ዘፋኝ በአንድ ወቅት ባወጣው አልበም ተስቦ የድምጻዊውን ማንነት በሚያጣራበት ወቅት ድምጻዊው የራሱ የጫማ ፋሽን ብራንድ እንዳለው ይገነዘባል።

12ተኛ ክፍል እያለን በትምህርት ቤታችን ራሳችንን የሚገልጽ ልብስ ለመሥራት ስንዘጋጅ ምን ዓይነት ልብስ ይሁን በሚለው ኤርሚያስ ያቀረበው ዲዛይን እና አንድ ጓደኛው ያቀረበው የዲዛይን ሃሳብ በጋራ በማጣመር አዲስ ዲዛይን ተሰራ። ከዚያም ልብስ ዲዛይን ወደ ማድረግ ሃሳብ መምጣቱን ተናግሯል።

እሱነቱን ይገልጻሉ የሚላቸው አለባበሶች እንደልብ አለማግኘቱ ኤርሚያስ ፋሽን ዲዛይንን ለመማር እንዲወስን አደረገው። ይህን ተከትሎም ‹‹ታሪዮ›› የሚለው እሳቤ ተመሠረተ ሲል ይገልጻል።

እሱ እንዳብራራው፤ ‹‹ ታሪዮ ›› የሚለው ቃል ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰደ ነው፤ ትርጉሙም ራስን በማወቅ የሚመጣ በራስ መተማመን አልያም ጎልቶ መታየት የሚል ነው። የሰዎችን እይታ መፈለግ፣ በሌሎች እይታ ውስጥ መግባት፣ በፋሽን ኢንዱስትሪው ጎልተው የሚወጡ ደማቅ የሆኑ



ቀለማት የሚሉትን እሳቤዎች ኤርሚያስ አይስማማባቸውም።

‹‹አንድ ሰው በራሱ ለመተማመን ራሱን በደንብ ማወቅ አለበት፤ ፋሽን ሰዎች ራሳቸውን የሚገልጹበት አንዱ መንገድ ነው ብዬ አስባለሁ። አንድ ሰው ራሱን በፋሽን ውስጥ ለመግለጽ ከማሰቡ አስቀድሞ ግን ራሱን በደንብ ማወቅ፣ ታሪኩን ማወቅ ይኖርበታል፤ እንደዚያ ካልሆነ ግን የሆነን ሰው መንገድ መከተል ይሆናል ›› ሲል ያብራራል።

የታሪዮ ፋሽን ዋና መገለጫ ‹‹ ፍርሀት የለም ›› የሚል ሃሳብን የያዘ መሆኑን ተናግሮ፣ ሰዎች ምንም የሚያስፈራቸው ሁኔታ ባይኖር ራሳቸውን በትክክል መግለጽ፣ አቅማቸውን አውጥተው ማሳየት ይችላሉ የሚል መልዕክት የሚያስተላልፍ ነው ሲል አመልክቷል።

‹‹ እኔ የማምነው አንድ ሰው ራሱን ይበልጥ እያወቀ እና እየተረዳ በመጣ ቁጥር የማንም ሰው ይሁንታ እና ማረጋገጫ አይፈልግም፤ በጣም እየተረጋጋ የሚመጣ እና የራሱን ትክክለኛ ባህሪ የሚገነባ በመሆኑ ባለው እይታ ራሱን የሚገልጽበት መንገድ ጎልቶ እንዲወጣ ያደርገዋል ›› ሲል ያብራራል፡፡

የ12ተኛ ክፍል ትምህርቱን አጠናቆ ለፈተና በሚዘጋጅበት ወቅት የዲዛይን ትምህርት መማር ጀመረ። ታሪዮ የሚለው የፋሽን ዲዛይን ሃሳብም እውን ወደ መሆን መጣ። በሰባት ወር የትምህርት ጊዜው ታሪዮ የሚለውን ብራንድ እንዴት መገንባት ይቻላል የሚለውን እና ቴክኒካል እውቀትን ቀሰመ።

የፋሽን ዲዛይን ተማሪዎች ተምረው ሲጨርሱ የራሳቸውን የፈጠራ ሥራዎች በምረቃ ቀናቸው ያቀርባሉ። ኤርሚያስም በዚህ ቀን ያቀረበው የዲዛይን ሥራ በብዙዎች ዘንድ አድናቆትን አተረፈለት። ‹‹በወረቀት ላይ ዲዛይን አድርጌ ለሰዎች ሳሳይ ብዙዎች አልወደዱትም ነበር፤ ተሰርቶ ሲያልቅ ግን ተቀበሉት›› ሲል ይገልጻል።

የታሪዮ ፋሽን በገበያ ላይ ተቀባይነት ያገኙ አልያም ገበያን መሠረት ተደርገው የሚሰሩ ልብሶችን በማውጣት ላይ አያተኩርም። ‹‹የምሰራቸው ልብሶች በሰዎች ዲዛይን ውስጥ ቶሎ የሚታዩ አይደሉም፤ ሰዎች በፈለጉበት ጊዜ የሚለብሷቸው፣ እንደፈለጉ ዲዛይን እንዲያደርጓቸውና በየእለቱ እንዲጠቀሙባቸው እፈልጋለሁ›› የሚለው ኤርሚያስ፣ በጊዜ የማይገደቡ የፋሽን ዲዛይኖችን ወደ ገበያው ይዞ መቅረቡን ተናግሯል። ‹‹እንደ ታሪዮ ኮሌክሽን ሳይሆን ሥራዎቻችንን ምዕራፍ ብለን ነው የምንገልጻቸው። በእያንዳንዱ ሥራዎቻችን ላይ ማስተላለፍ ከምንፈልገው ታሪክ ጋር ነው የምናጋራው። ››

ለመጀመሪያ ጊዜ ሰርቶ ያስተዋወቀው የፋሽን ዲዛይን ስብስብ በእርሱ አጠራር ምዕራፍ ‹‹አልኬቡላን›› የሚል ስያሜ የተሰጠው ነው። ‹‹አልኬቡላን አውሮፓውያን ወደ አፍሪካ አህጉር ከመምጣታቸው በፊት አህጉሪቱ ትጠራበት የነበረው ስም ነው። ትርጉሙ የሰው ዘር መገኛ ማለት ነው። በዚህም የመጣንበትን መንገድ እንወቅ የሚል መልእክት አስተላልፏል። ለእዚህም ለአፍሪካ ትልቅ ዋጋ የከፈሉ እንደ ኔልሰን ማንዴላ ያሉ የነፃነት ታጋዮችን እንደ ምሳሌ ተጠቅመናል ›› ሲል ገልጿል።

የፋሽን ዲዛይን ሥራዎች በአብዛኛው የሚተዋወቁት በሴቶች ነው። ኤርሚያስ ግን ሃሳቡን በልብስ ዲዛይኖች ላይ ማሳረፍ የጀመረው በወንዶች ነው። ‹‹ታሪዮ ፋሽን ገበያውን የተከተለ አይደለም፤ አዲስ ነገር ሰርቶ ለዛ የሚሆን ገበያን መፍጠር እፈልጋለሁ፡፡›› ይላል።

ኤርሚያስ ሥራዎቹን ለማስተዋወቅ ታዋቂ ሰዎችን አልያም የፋሽን ዲዛይን ሞዴሎችን አይጠቀመም። ሃሳቡ ሰዎች ታዋቂ ሰው ስለለበሰው አይተው እንዲለብሱት አይደለም። ራሳቸውን አውቀው ስታይላቸውን ፈልገው ማንነታቸውን እንዲለብሱት ነው።

የታሪዮ ፋሽን ሃሳብ ከተመሰረተ ሁለት ዓመት ያህል እድሜ አስቆጥሯል። ዲዛይን የሚያደርግበት መንገድ ታሪዮ የሚለውን ሃሳብ ሊገልጹ ይችላሉ የሚላቸውን አለባበሶች ከገበያ የማይወጡ አልያም በዚህ ጊዜ ያበቃሉ የማይባሉ ዲዛይኖች እና ሰዎች በማንኛውም ወቅት እና ጊዜ ሊለብሷቸው የሚችሏቸውን ልብሶች ነው።

ታሪዮ ራሱን የቻለ የአኗኗር ዘይቤ እንዲሆን እንደሚፈልግ ጠቅሶ፣ ሰዎች በየእለቱ የሚገለገሉባቸውን እንደ የሸክላ፣ የእንጨት ሥራዎች ያሉትን የእደ ጥበብ ውጤቶች በቤት ማስዋብ ላይ ማሳረፍ እንደሚፈልግም ይናገራል።

ዲዛይን ስሜት ላይ ተጽእኖ የማሳደር ውሳኔን የማሳደር ትልቅ አቅም እንዳለው ተናግሮ፣ ትልቁ አላማዬ ሰዎች ራሳቸውን እንዲያውቁ በራሳቸው እንዲተማመኑ ማድረግ ነው፤ በመሆኑም ተመሳሳይ የሆነ ውበት እና መልዕክት ያላቸውን ሃሳቦች እቃዎችና ቤቶች ላይ ዲዛይን ማድረግ እፈልጋለሁ ብሏል።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## የሞተር ሳይክሎቹ ነገር...

**አልማዝ አያሌው**

ከቢሮዬ ብዙም በማይርቁ ህንፃዎች፣ በየፎቁ ማረፊያ ላይ ዘወትር የሚታየው የቡና አቀራረብ ይማርካል። እሱን ተከትሎ በወጉ ከሚቆላው ቡና ለአፍንጫ የሚደርሰው ልዩ መዓዛ ፣ የሻይ ቅመም ሽታ ... ብቻ ምን አለፋችሁ ቦታውን አልፎ ለመሄድ በእጅጉ ይፈትናል።

በተለይማ ‹‹ሱስ›› አለብኝ ለሚል ቡና አዘውታሪ የሚያየውን አልፎት ሊሄድ ይቸግረዋል። ከቀናት በአንዱ አብረውኝ ከነበሩት መካከል አንደኛዋ "ኧረ ይሄንን ቡና ማለፍ ..." ትንሽ የሆነ ቃላት ወረወረች። ሁላችንም ተያይተን ፈገግ አልን። ምክንያቱም ቀሪዎቻችን የማኪያቶ እንጂ የቡና አፍቃሪዎች አይደለንም። ያም ሆኖ ቡና ፉት አንልም ማለት አይደለም። ስለዚህ የምንጠጣውን ቁጭ ብለን ለመወሰን ግብዣውን መቀበል ግድ ነውና ተስማማን።

ረፋድ ላይ የቡና ሰዓት ነው ልበል? ከዚህም ከዛም በሚመጡ እንግዶች ወንበሮቹ ተይዘዋል። በወጉ ተደረደሩ አነስ አነስ ያሉ ወንበሮችን ሳብ አድርገን ተቀመጥን። በጋራ ቡና ለመጠጣት የተቀመጡት የየራሳቸውን ጨዋታ ይዘዋል። ከወንዱም፣ ከሴቱም ተደበላልቀው፣ በርከት ብለው አጠገባችን የተቀመጡ ወጣቶች ይታያሉ። ጀርባቸውን ሰጥተውናል። ጨዋታቸው ጆሮ ገብ ነውና ልቤን እየሰረቀው ነው።

እንደው ለወጉ ከጓደኞቼ ጋር በአካል ተቀመጥኩ እንጂ በጨዋታ ማዳመጡ ተሳታፊ የነበርኩት ከወደኋላዬ ነው። በአካል እዚህ፣ በጨዋታ ደግሞ እዛ። ቀልቤን የሳበው ጭውውታቸው አሁን አሁን የከተማውን ነዋሪ እያስፈራ ያለው በሞተር ሳይክል የሚደረግ ዝርፊያ ነው። እኔ አሁንም ጆሮዬን ጥያለሁ፡፡

"ሰማሽ እንዴ...›› አንዷ ጨዋታዋን ቀጠለች። "ምኑን... ?›› አጠገቧ ያለችው እንደኔ ጆሮዋን ጣለች"

"እዛ ኮንዶሚኒየሙ ጋር የሚመላለሰው ሞተር ሳይክል እኮ ሥራው... " ስትል አዳማጭዋ ብዙ አላስኬደቻትም። እሷም በተደጋጋሚ የሰማችው ወሬ መሆኑን አከለችበት። ‹‹እንደውም እኮ! ለፖሊስ ወንጀሉ ሲጠቆም ‹‹በማስረጃ አስደግፋችሁ አምጡ እጅ ከፍንጅ ካልሆነ ተብለው ነዋሪዎቹ ‹‹ኩም›› ተደረጉ አሉ›› ወሬውን ቀጠለች። ... ጨዋታው ደርቷል። ሁሉም የሰማውን ሁሉ ያብራራ ጀመር። የአንዳንዱ ጨዋታ ከ "አሉ " አለፍ ያለ ነው። በተጨባጭ የተያዙትና በፖሊስ የቴሌቭዥን ፕሮግራም ያዩ፣ የሰሙትን አክለው ነው የሚያወሩት።

‹‹ኧረ ! የሌባ ነገር በጣም አስፈሪ ሆኗል። በሞተር ሳይክል እያለፉ አንገቱ ላይ ወርቅ አድርጎ ያዩትን ወጣት መሀል ከተማ ላይ መንትፈውት ማምለጣቸውን ፤ ከጆሮ ላይ ሞባይል፣ ከሴቶች ትከሻ ቦርሳ እየተመነተፈ መሆኑ በማብራሪያ ተገለጸ። አስፈሪና አሳዛኝ በሆነ መልክ በከተማችን እየሆኑ ያሉ ችግሮችን የሚገለጽ ስጋት አዘል ወሬ ከዚህም ከዛም ይዋጣል።

እኔም በአንድ ወቅት በሞተር ሳይክል ታጅቦ የተደረገ አንድ የዝርፊያ ሙከራ ትውስ አለኝ። "አይደፈሬ" በሚባል ቤተክርስቲያን ላይ የተሞከረ ነበር። በጊዜው በመሳሪያ ታግዘው ዝርፊያ ሊፈጽሙ የነበሩ ሶስት ታርጋ የሌላቸው ሞተር ሳይክሎች በዓይነ ህሊናዬ ግጥም አሉ። በቤተክርስቲያኑ ሠራተኞችና አስተዳደሪዎች በተሰበሰቡበት ቢሮ ውስጥ ያጋጠማቸውን አሳዛኝ ድርጊት የገለጹትም "ወዴት እየሄድን ነው" ሲሉ ነበር ። የአሁኑ የሰዎች ጭውውትም ወደ እዛው እውነታ ወሰደኝ። "ወደየት እየሄድን ነው?"››

በሞተር ሳይክል የሚደረገው ውንብድና በዚህ ብቻ የሚያቆም እንዳልሆነ ደግሞ አንድ ባልደረባዬ ነግሮኝ ነበር። ምነው ፖሊሶቻችን የት ናቸው? ምንስ እየሰሩ ነው? ለማለት አስደፈረኝ። ነገሩ እንዲህ ነው።

> **ይህ ሰው ሁሌም "ጫት ይዘህ ና" ይባላል፡፡ የጫቱ ስያሜ በጥቁር ገበያ የሚመነዘረውን የገንዘብ ዓይነት የሚያሳውቅ ኮድ አለው፡፡ የአወዳይ፣ የባህር ዳር ፣ የገለምሶ፤ ፓውንድ ፣ ዶላር ፣ ዩሮ... እንደ ማለት ነው፡፡ በዚህ ኮድ የተደወለለት ቦታ ላይ ገንዘብ ይዞ ይመጣል፣ ሥራውን ይፈጽማል**

አንድ በወጣትነት ዕድሜ ክልል ላይ ያለ ሞተረኛ ደጋግሞ ኮንዶሚኒየም አካባቢ ይመላለሳል። እንዲህ የሚያደርገው ታዲያ የውጭ ሀገር ገንዘቦችን በጥቁር ገበያ በመመንዘሩ ነው። እግር የማብዛቱ ሸፋን ደግሞ በብዙዎች የተለመደው ጫት ነበር።

ይህ ሰው ሁሌም "ጫት ይዘህ ና" ይባላል። የጫቱ ስያሜ በጥቁር ገበያ የሚመነዘረውን የገንዘብ ዓይነት የሚያሳውቅ ኮድ አለው። የአወዳይ ፣ የባህር ዳር ፣ የገለምሶ ፤ ፓውንድ ፣ ዶላር ፣ ዩሮ... እንደ ማለት ነው። በዚህ ኮድ የተደወለለት ቦታ ላይ ገንዘብ ይዞ ይመጣል፣ ሥራውን ይፈጽማል።

በዚህ ተግባር ተጠምዶ ሲመላለስ ታዲያ አንድ ፖሊስ ቢጠራጠር አስቁሞ ይፈትሸዋል ። ሞተር ሳይክሉን ብጥር አድርጎ ጫማውን ሳይቀር ይበረብርና ምንም ስላለገኘበት ይለቀዋል። አጅሬ ግን የመነዘረውን የውጭ ገንዘብ የከተተው የደህንነት መጠበቂያ (ሄልሜቱ) ውስጥ ኖሯል። "ዛሬ ገብቼለት ነበር፤ ግን አፈዘዝኩት" " እያለ ያመለጠበትን መንገድ እንደ ጀብዱ ያወራዋል።

‹‹ዛሬ ተሳከቶልህ ይሆናል ነገ ግን መያዝህ አይቀርም››አልኩ። በልቤ። ባለ ሞተር ሳይክሎች ከሚሰሩት ሕገ ወጥ ተግባር ባልተናነሰም ለነፍስ አድን ሥራዎችም የሚፈጥኑ ጥቂቶች አይደሉም። ሁሉም ወንጀለኞች ናቸው ባይባልም ጥሩ የሚሰሩትን ማመስገን ደግሞ ያስፈልጋል። መድኃኒት አለበት ከተባለ ቦታ ለህመምተኛ ፈጥነው ያደርሳሉ። በየመንገዱ የሚቆሙ መኪናዎችን የሚጠግን የጋራዥ ሠራተኛ በፍጥነት አምጥተውም መኪናውን ያሰራሉ። ለላቦራቶሪ ምርመራ የሚሄድ ናሙና በፍጥነት ሲያደርሱና ውጤት ሲያቀብሉ ለተመለከታቸው አንጀት አርስ ብሎ ያመሰግናቸዋል።

የኦን ላይ ገበያ ምርቶችን ለገዢው በማስረከብም ሚናቸው ከፍ ያለ ነው። እነሱን ታዲያ ኑሮ አቅላይ፣ ፈጥኖ ደራሽ ‹‹ከተፎ›› ማለት ይቻላል። ይሁን እንጂ ሕጋዊ የሆኑትን ብቻ አይቶ መዘናጋት ደግሞ አያስፈልግም። ተገቢው ክትትል ተገቢው ቁጥጥር ያስፈልጋል።

በመንገድ ላይ በእጅ ስልክ የሚያወሩትም ከአስፋልት ዳር ራቅ ብለው ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ ቢጠቀሙ ንብረታቸውን ከመንታፊዎች ያድናሉ። አሁን አሁን እየበረታ ያለው የሞባይል መንታፊ በእግረኛም፣ በሞተረኛም መሆኑን ልብ ማለት ይገባል። እኔ ደግሞ አይቼና ሰምቼ ከታዘብኩት ለመረጃም፣ ለትምህርትም ይሆን ዘንድ ይህን አልኩ ። ቸር እንሰንብት !

# ዓለም አቀፍ



## ኢራንና ሩሲያ  በህንድ ውቅያኖስ ላይ ወታደራዊ ልምምድ አካሄዱ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ኢራንና ሩሲያ  በህንድ ውቅያኖስ ላይ ወታደራዊ ልምምድ አካሄዱ።

ሩሲያ እና ኦማንን ያሳተፈ በኢራን የተዘጋጀው የባህር ኃይል ወታደራዊ ልምምድ በትናንትናው እለት መጀመሩን ሮይተርስ የኢራን መንግሥት መገናኛ ብዙኃንን ጠቅሶ ዘግቧል።

እንደዘገባው ከሆነ በልምምዱ ላይ ዘጠኝ ሀገራት በታዛቢነት ተጋብዘዋል።

“አይኤምኢኤክስ 2024” የተሰኘው የዚህ ልምምድ አላማ በቀጣናው የጋራ ደህንነትን ለማረጋገጥ እና የማሪታይም ደህንነትን ለመጠበቅ ወዳጅነትን ለማሳየት መሆኑን ሮይተርስ ዘግቧል።

የልምምዱ ተሳታፊዎች የዓለም አቀፍ የንግድ ደህንነት በማስከበር፣ የባህር መስመሮችን በመከላከል፣ የሰብአዊ ሥራዎችን በማጠናከር እና በነፍስ አድን እና የእርዳታ አቅርቦትን በማጠናከር ዙሪያ ልምምድ ያደርጋሉ።

ልምምዱ  እስራኤል በጋዛ እየወሰደች ያለው እርምጃ ማየልን እና በኢራን የሚደገፈው የየመኑ ሀውቲ ታጣቂ በመርከቦች ላይ ጥቃት በመሰንዘር የአጸፋ ምላሽ መስጠቱን ተከትሎ ከተፈጠረው ቀጣናዊ ውጥረት ጋር ተገጣጥሟል።

ኢራን በቀጣናው ከአሜሪካ ጋር ለገባችበት ውጥረት ከሩሲያ እና ቻይና ጋር ወታደራዊ ትብብር በማድረግ ምላሽ እየሰጠች ነው።

ባለፈው ሚያዝያ ወር ኢራን፣ ቻይና እና ሩሲያ አምስተኛ የጋራ የባህር ኃይል ልምምዳቸውን በኦማን ባህረሰላጤ ማካሄዳቸው ይታወሳል።

ሳኡዲ አረቢያን፣ ኳታር፣ ህንድ፣ ባንግላዴሽ እና ታይላንድን ጨምሮ ሀገራት የአሁኑን ወታደራዊ ልምምድ እየተመለከቱ ናቸው።

ኢራን የሊባኖስን ወረራ እና የሄዝቦላህ መሪ ነስረላህ ግድያን ለመበቀል በእስራኤል ላይ የሚሳይል ናዳ ማዝነቧ ይታወሳል።

ይህን ተከትሎም እስራኤል በኢራን ላይ የአጸፋ እርምጃ እንደምትወስድ ዝታለች።



## የእስራኤልን የማጥቃት እቅድ የሚያሳይ ምስጢራዊ ሰነድ ከአሜሪካ ደህንነት ሾልኮ መውጣቱ ተዘገበ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አሜሪካ ሰነዱ እንዴት እንደወጣ ምርመራ እያካሄደች ነው ተብሏል።

የእስራኤልን የማጥቃት እቅድ የሚያሳይ ምስጢራዊ ሰነድ ከአሜሪካ ደህንነት ሾልኮ መውጣቱ ተዘገበ።

እስራኤል በኢራን ላይ የምትፈጽመውን የበቀል ጥቃት እቅድ ያሳያል የተባለ ጥብቅ ምስጢራዊ ሰነድ ከአሜሪካ ደህንነት ሾልኮ ወጥቷል ተብሏል።

አሜሪካ፣ እስራኤል ልትፈጽመው የምትችለውን የማጥቃት እቅድ የሚዳስሰው ምስጢራዊ ሰነድ እንዴት እንደወጣ ምርመራ እያካሄደች መሆኑን ኤፒ ሶስት የአሜሪካ ባለስልጣናትን ጠቅሶ ዘግቧል። ኤፒ ያናገራቸው አራተኛው የአሜሪካ ባለስልጣን ሰነዱ ትክክለኛ ይመስላል ብለዋል።

ሰነዶቹ የወጡት ከአሜሪካ ጂኦስፓሺያል ኢንተለጀንስ ኤጀንሲ ሲሆን፤ እስራኤል ኢራን ባለፈው ጥቅምት አንድ ለፈጸመችባት የባለስቲክ ሚሳይል ጥቃት ምላሽ ለመስጠት መሳሪያዎቿን ጥቃት ለመፈጸም ወደሚያስችል ቦታ ማንቀሳቀሷን ጠቅሷል።

ሰነዶቹ “አምስት አይኖች” ለተባሉት ለአሜሪካ፣ ብሪታኒያ፣ ካናዳ፣ ኒውዝላንድ እና አውስትራሊያ መጋራት የሚችሉ ናቸው።

ጥብቅ ምስጢራዊ መረጃ የሚል የተጻፈባቸው ሰነዶች በቴሌግራም የተጋሩ ሲሆን፤ ለመጀመሪያ ጊዜ የተዘገበው በአሜሪካው የሲኤንኤን ቴሌቪዥን ነው።

ሰነዶቹ ሆን ተብሎ በአሜሪካ የስለላ ሰራተኞች ወይም በጠለፋ ስለመውጣታቸው እና ሌሎች የሾለኩ ምስጢሮች ስለመኖራቸው ምርመራ እየተካሄደ መሆኑን ኤፒ ያናገራቸው እና ስማቸውን ያልገለጻቸው ባለስልጣን ተናግረዋል።

እኝህ ባለስልጣን ፖስት ከማድረግ በፊት ሰነዶቹን ማግኘት የሚችለው ማነው የሚለውን ለመወሰን ምርመራ እየተካሄደ ነው ብለዋል።


ሰነዶቹ የወጡት አሜሪካ፣ እስራኤል የሀማስ መሪ ያህያ ሲንዋርን መወገድ ጫና ለመፍጠር እንድትጠቀምበት እና በሰሜን ሊባኖስ ያለውን ጦርነት እንዳታስፋፋ እና ቀጣናዊ ጦርነት እንዳይቀሰቀስ ጥንቃቄ እንድታደርግ እያሳሰበች ባለችበት ወቅት ነው።

ነገር ግን የእስራኤል አመራር የኢራን የሚሳይል ጥቃት ምላሽ ሊሰጠው እንደሚገባ በተደጋጋሚ ተናግረዋል።

የአሜሪካ መከላከያ ሚኒስቴር ፔንታጎን ባወጣው መግለጫ ስለሰነዶቹ መረጃው እንዳለው ገልጿል።

ኢራን የሊባኖስ ወረራ እና የሄዝቦላህ መሪ ግድያ ሀሰን ነስረላህን ግድያ ለመበቀል በእስራኤል ላይ የሚሳይል ናዳ ማዝነቧ ይታወሳል።

# ስፖርት



# የወጣት እጅ ኳስ ብሔራዊ ቡድኑ ለአፍሪካ ቻምፒዮና እየተዘጋጀ ነው

ዓለማየሁ ግዛው

የአፍሪካ ከ18 እና 20 ዓመት በታች ወንዶች እጅ ኳስ ቻምፒዮና ከጥቅምት 23 እስከ 27/2017 ዓ.ም በኢትዮጵያ አስተናጋጅነት በወጣቶች ስፖርት አካዳሚና አራት ኪሎ ትምህርትና ስልጠና ማዕከላት ጅምናዝየሞች ይካሄዳል። በውድድሩ ኢትዮጵያን ጨምሮ ከየዞኑ የተወከሉ 12 ሀገራት ለዓለም እጅ ኳስ ዋንጫ ለማለፍ የሚፋለሙ ሲሆን የኢትዮጵያ ወጣት ብሔራዊ ቡድንም ከወዲሁ ዝግጅቱን ጀምሯል፡፡

የዓለም እጅ ኳስ ፌዴሬሽን ከአፍሪካና የኢትዮጵያ እጅ ኳስ ፌዴሬሽኖች ጋር በትብብር የሚያዘጋጁት የ2024 የአፍሪካ ከ18 እና 20 ዓመት በታች ወንዶች እጅ ኳስ ቻምፒዮና ለአንድ ሳምንት ይካሄዳል። ኢትዮጵያ ከወራት በፊት በዞን ደረጃ የተካሄደውን ከ18 እና 20 ዓመት በታች ወጣትና ታዳጊዎች እጅ ኳስ ቻምፒዮናን ማስተናገዷ የሚታወስ ሲሆን፣ አህጉር አቀፉንም ውድድር በስኬት ለማስተናገድ በዝግጅት ላይ ትገኛለች። ውድድሩን ከማስተናገድ ባሻገር ከ18 ዓመት በታች እጅ ኳስ ብሔራዊ ቡድኑ ተሳታፊ በመሆኑ ኢትዮጵያ ጠንካራ ተፎካካሪ ሆና ለመቅረብ የሚያስችላትን ዝግጅት እያደረገች ትገኛለች።

በአፍሪካ እጅ ኳስ ቻምፒዮና ለመጀመሪያ ጊዜ መሳተፉን ያረጋገጠው የኢትዮጵያ ከ18 ዓመት በታች እጅ ኳስ ብሔራዊ ቡድን በቅርቡ አሰልጣኝ እና የቡድን መሪ ተመድቦለት ዝግጅት እያደረገ ነው። በዋና አሰልጣኝነት ኢንስፔክተር ተስፋዬ ሙለታ እንዲሁም በምክትል አሰልጣኝነት ጃቢር ሽምሱ ቡድኑን ለአፍሪካ ዋንጫ ማሳለፋቸው የሚታወቅ ሲሆን በአህጉር አቀፉ መድረክም ውጤታማ ለመሆን ቡድኑን እያዘጋጁት ይገኛሉ። የፌዴሬሽኑ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ ሰጠኝ አዲሱ ደግሞ የቡድኑ መሪ ናቸው፡፡




**የኢትዮጵያ ከ18 ዓመት በታች እጅ ኳስ ብሔራዊ ቡድን፣**

ኢትዮጵያ ከአምስት ወራት በፊት ከዓለም እጅ ኳስ ፌዴሬሽን እና ከአፍሪካ እጅ ኳስ ፌዴሬሽን ጋር በትብብር ባዘጋጀችውና 11 የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት የተሳተፉበት የዞን 5 ከ18 እና ከ20 ዓመት በታች እጅ ኳስ ቻምፒዮናን በስኬት ከማስተናገዱ በተጨማሪ ብሔራዊ ቡድኗም ጠንካራ ተፎካካሪ መሆን ችሎ ነበር። በወቅቱ ብሔራዊ ቡድኖቹ በብዙ ፈተናዎች ውስጥ ሆነው ዝግጅታቸውን ቢያደርጉም፣ ከ20 ዓመት በታች ቡድኑ ሦስተኛ ደረጃን ይዞ ሲያጠናቅቅ ከ18 ዓመት በታች ቡድኑ ደግሞ ዋንጫው ማንሳት ችሏል።

ከ18 ዓመት በታች ብሔራዊ ቡድኑን ለዚህ ስኬት ያበቁት አሰልጣኞች አሁንም በአፍሪካ ቻምፒዮና ውጤታማ ለመሆን ጥቅምት ከ8/2017 ዓ.ም ጀምሮ ቡድኑን አሰባስበው ዝግጅት የጀመሩ ሲሆን፣ የተመረጡና በክለብ ውድድር ምክንያት ውጪ ሀገር የሄዱ ስድስት ተጫዋቾችን በማካተት ጠንካራ ዝግጅት እንሚያደርጉ ዋና አሰልጣኙ ኢንስፔክተር ተስፋዬ ሙለታ ገልጸዋል። በዚህም መሠረት ለዝግጅቱ 18 ተጫዋቾች የመጀመሪያ ጥሪ ተደርጎላቸው ዝግጅት ሲጀምሩ በሂደት አራት ተጫዋቾች እንደሚቀነሱም ታውቋል፡፡

አብዛኞቹ ተጫዋቾች ከእረፍት እንደመመለሳቸው ለስድስት ቀናት ጠዋት እና ማታ የአካል ብቃትን መሠረት ያደረገ ዝግጅት እንደሚደረግ አሰልጣኙ ጠቁመዋል። ከ18 ዓመት በታች ከሚገኘው ብሔራዊ ቡድን ውስጥ ሦስት ተጫዋቾች ተቀንሰው እድሜያቸው ገና የሆኑ ሦስት ተጫዋቾች ደግሞ ከ20 ዓመት በታች ብሔራዊ ቡድን ውስጥ መካተታቸውንም ተናግረዋል። ለአንድ ሳምንት ያህል የአካል ብቃትንና ትንፋሽን መሠረት ያደረገው ልምምድ ከተጠናቀቀ በኋላም የቡድን ቅንጅት ላይ የሚሰራ ይሆናል ብለዋል።

ውድድሩ ኢትዮጵያ እንደ መካሄዱ ዋንጫ ለማንሳት ጠንካራ ዝግጅት እንደሚደረግ የገለፁት አሰልጣኙ፣ ቡድኑ በቂ ዝግጅት በማድረግ ተፎካካሪ ሆኖ እንዲቀርብ አስፈላጊው ድጋፍና ምቹ ሁኔታ መፈጠር እንዳለበትም አሳስበዋል፡፡

በስድስቱ አፍሪካ ዞን ውድድሮችን አድርገው አሸናፊ የሆኑ ከ18 እና 20 ዓመት በታች ሁለት ቡድኖች በአጠቃላይ አሥራ ሁለት ቡድኖች በአህጉር አቀፉ ቻምፒዮና የሚፋለሙ ይሆናል። በታዳጊዎች ኢትዮጵያ፣ ካሜሩን፣ ጊኒ፣ ማዳጋስካር፣ ናይጄሪያ እና ዚምባብዌ የሚሳተፉ ሲሆን፣ በወጣቶች ኮንጎ ጋና፣ ጊኒ፣ ርዋንዳ እና ዚምባብዌ ተሳታፊ ሀገራት ናቸው። በሁለቱም የእድሜ እርከኖች የሚያሸንፉ ሀገራት አፍሪካን ወክለው በዓለም እጅ ኳስ ቻምፒዮና ላይ ይሳተፋሉ፡፡

ኢትዮጵያ እጅ ኳስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ዶክተር ፍትሕ ወልደሰንብት በፌዴሬሽኖች ጥረት ውድድሮች ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡ ቢሆንም ብዙ ትኩረት ይሰጥ እንዳልነበረ አስታውሰው፣ አሁን ግን በመንግሥት ልዩ ትኩረት እየተሰጠ እንደሚገኝ ተናግረዋል። ውድደሩን ኢትዮጵያ ለማዘጋጀት የተፈለገችውም የሀገሪቱን መልካም ገጽታ ለመገንባት እና ሕዝብ ለሕዝብ ትስስሩን ለማጠናከር እንደሆነ ገልጸዋል። የእጅ ኳስ ፕሪሚየር ሊግ በመኖሩ ታዳጊዎችን ለማነሳሳትና ብሔራዊ ቡድን የመጫወትና የውድድር እድልን ለመፍጠር ትልቅ ሚና እንዳለውም አክለዋል። ለውድድሩ ከ350 በላይ ልዑካኖች ወደ አዲስ አበባ የሚመጡ ሲሆን በመድረኩ የአፍሪካ እጅ ኳስ ፌዴሬሽን ኢትዮጵያ ላይ አካዳሚ የመክፍት እቅዱን እንዲቀጥልበት ለማሳመን ይሰራልም ተብሏል፡፡